


# የመተዳደሪያ ደንብ

በሳናንቶኒዮ የኢትዮጲያንና የኤርትራውያን ቤተ ክርስትያን   ክርስትያኖች ህብረት

# ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| መግቢያ | 3 |
| የቤተክርስቲያን የድርጅት መዋቅር (Organizational Chart) | 4 |
| የድርጅቱ ስም | 5 |
| ጽሕፈት ቤቶች | 5 |
| መሠረተ-እምነት እና የእምነት አንቀጽ | 5 |
| ዓላማ | 12 |
| ወገናዊነት የማይንጸባረቅባቸው እንቅስቃሴዎች | 14 |
| ቤተክርስቲያንና ግንኙነት | 14 |
| አገልጋዮች | 15 |
| የሽማግሌ ብቃት | 16 |
| የሽማግሌ ምርጫ | 17 |
| የሽማግሌ የአገልግሎት ዘመን | 17 |
| የሽማግሌዎች ቦርድ የሥራ ሃላፊነትና ተግባር | 17 |
| የሽማግሌዎች ቦርድ ስብሰባ | 19 |
| የሽማግሌ መገለል ወይም ስንብት | 19 |
| የሽማግሌዎች ቦርድ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ የሥራ ኃላፊነት | 20 |
| የሽማግሌዎች ቦርድ ጸሐፊ | 20 |
| የዲያቆናት ብቃት | 21 |
| የዲያቆናት ምርጫና የአገልግሎት ዘመን | 21 |
| የዲያቆናት የሥራ ኃላፊነትና ተግባር | 22 |
| የዲያቆናት መገለል ወይንም ስንብት | 23 |
| የእረኛው ብቃትና ችሎታ | 23 |
| የዋና እረኛው የሥራ ኃላፊነትና ተግባር | 24 |

ሹመት ....................................................................................................................................................25

የእረኛው መብት ..........................................................................................................................................25

የአገልግሎት ዘመን .....................................................................................................................................26

ከሥራ የመገለል ሁኔታዎች (ምክንያቶች) ..........................................................................................26

ተባባሪ እረኛ (Associate Pastor)............................................................................................................26

ቤተክርስቲያን ያለ ዋና እረኛ በምትሆንበት ጊዜ .............................................................................27

የወጣት አገልግሎት ....................................................................................................................................27

የወጣት መጋቢ ብቃትና ችሎታ ..............................................................................................................29

ከሥራ የመገለል ሁኔታዎች (ምክንያቶች) ..........................................................................................30

አባልነት ......................................................................................................................................................30

የአባላት መብትና ግዴታ ...........................................................................................................................31

ከአባልነት የመገለል (የመሰረዝ) ምክንያት ..........................................................................................32

የአስተዳደር፥ ፋይናንስና የገንዘብ ያዥ ኃላፊነት ..............................................................................32

የመረዳጃ እድር ..........................................................................................................................................33

የገንዘብ አያያዝና አወጣጥ ......................................................................................................................34

የሂሳብ ምርመራ ..................................................................................................................................... 35

ደንቡን የማሻሻል ይዘት ..........................................................................................................................35


ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ ...............................................................................................................................36

ትርጉም ......................................................................................................................................................36

# መግቢያ

ለእግዚአብሔር ሕዝብ ማለትም ለቤተ ክርስቲያን መመሪያ የሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰፈረው የእግዚአብሔር ቃል መሆኑ የታወቀና የታመነ ነው። ቤተክርስቲያን እንደ ድርጅት ተግባራዊ ለምታድርጋቸው ዓላማና እቅዶቿ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ የመተዳደሪያ ደንብ የሚያስፈልጋት ስለሆነ የመተዳደሪያ ደንቡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳቦችን መሰረት በማድረግ እንዲሁም ከአንዳንድ የቤትክርስቲያኒቱ አባላት የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተዘጋጅቷል።

# Organization Chart



## አንቀጽ 1

## የድርጅቱ ስም

ሀ) የድርጅቱ ስም በሳናንቶኒዮ የኢትዮጲያንና የኤርትራውያን ቤተ ክርስትያን   ክርስትያኖች ህብረት ይሆናል።

ለ)  ድርጅቱ በቴክሳስ  የባፕቲስት ጀነራል ኮንቪንሽን አባል ነው።

## አንቀጽ 2

## ጽሕፈት ቤቶች

2.1 ዋና ጽሕፈት ቤት

የድርጅቱ ጉዳዮች ማስፈጽሚያ ዋና ጽ/ቤት በሳናንቶኒዮ ይሆናል። የሽማግለዎች ቦርድ (ማለትም የቤተክርስቲያኒቱ ዋና እረኛና ሽማግለዎች) የድርጅቱን ዋና ጽ/ቤት **አባላቱን ካስጸደቀ በኋላ** ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ማዛወር ይችላል። የተደረገውንም የአድራሻ ለውጥ ይህ ደንብ ለተላከለት የመንግሥት አካል በጽሁፍ ይገልጣል።

2.2 ሌሎች ጽ/በቶች

ይህ ድርጅት በሽማገለዎች ቦርድ አማካኝነት ተግባሩን ማካሄድ በሚችልበትና በተፈቀደለት በማንኛውም ስፍራ የዋናው ጽ/ቤት ቅርንጫፍ የሆኑ ሌሎች የወንገል ስርጭት ጽ/ቤቶችንና አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን መክፈት ይችላል። በሂደት አጥቢያዎቹ እራሳቸውን እንዲችሉ ያደፋፍራል፤ ይረዳል፤ ይደግፋልም።

## አንቀጽ 3

## መሠረተ-እምነት እና የእምነት አንቀጽ

3.1 መጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይና አዲስ ኪዳን 66ቱ መጻሕፍት በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው ቅዱሳን ሰዎች እንደጻፉት ሊታመንበት የሚገባ የቤትክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ምንጭና መለኪያ የሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ

ያለበት ለትምህርት ለተግሳጽና ልብን ለማቅናት በጽድቅም ላለ ምክር የሚጠቅም ብቃት ኃይልና ሥልጣን ያለው እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ታምናለች። 2ኛ ሳሙ 23:2፥ መዝ 12:6፥ ማቴ 24:35፥ ዮሐ 17:17፥ 1ኛ ተሰ 2:13፥ 2ኛ ጢሞ 3:15-17፥ ዕብ 4:12፥ 2ኛ ጴጥ 1:20፥ ያዕቆብ 1:25፥ ራዕይ 22:8-9።

## 3.2 እግዚአብሔር

በሰማይና በምድር የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ በፈጠረ ፍፁም ህያው ሁሉን ቻይ ዘላለማዊ የማይወሰን ያማይለወጥ ራሱን በሶስት አካል በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ በገለጠ በአንድ አምላክ ታምናለች። ይኸውም አካላቱን ሳትደባልቅ መለኮታዊ ሕልውናውን ሳትከፍል ነው። ዘፍ 1:26፥ 3:22፥ 17:1፥ ዘዳ 6:4-5፥ መዝ 90:2፥ 139፡ 7-12፥ ኢሳ 40:28፥ 48:12-16፥ ሚል 3:6፥ ማቴ 5:48፥ ዮሐ 17:11፥የሐዋ 17:24፥

### 3.2.1 እግዚአብሔር አብ

እግዚአብሔር አብ በፍቅሩ ለአዳም ዘር በገባው ቃል ኪዳን መሰረት የሰጠውን የተስፋ ቃል በመጠበቅ ለሰብአዊ ፍጡር ሁሉ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደህንነት እንዳዘጋጀ ኃጢአታቸውን ተናዘው አንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ለሚቀበሉት ሁሉ ልጆቹ ይሆኑ ዘንድ ስልጣን እንደሰጠ ታምናለች። ዘፍ 3:1-24፥ 12:1-3፥ 17:1-2፥ 22:16-18፥ ዘፀ 3:15፥ ዘፀ 6፡2-5፣ ዮሐ 1:12፥ 1:19፥ 3:16፥ ኤፌ 4:6፥

### 3.2.2 እግዚአብሔር ወልድ

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ ዘላለማዊ ልጅ መሆኑን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተፀንሶ ከድንግል ማርያም መወለዱን ፍፁም አምላክና ፍፁም ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም መምጣቱን ኃጢአት ያልሰራ የኃጢያተኞች ምትክ ሆኖ መሞቱን በመስቀል ላይ ደሙን በማፍሰስ ለኃጢያት ቤዛ አድርጎ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቁን ከሞት ተነስቶ በክብር ማረጉን በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጦ ለእኛ ሊማልድ ዘወትር በሕይወት መኖሩን የቤተክርስቲይን ራስና መስራች መሆኑን በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ዳግመኛ በክብር እንድሚመጣ ታምናለች። ዘፍ 3:15፥ ኢሳ 53:1-12፥ ማቴ 16:18፥ ሉቃስ 1:26-35፥ ዮሐ 1:14-18፥ የሐዋ 17:31፥ 7:21፥ 13:8፥ 2ኛ ቆሮ 5:18-21፥ ኤፌ 1:22-23፥ 2:13-18፥ ፊሊ 2:6-7፥ 1ኛ ጢሞ 3:16፥ ዕብ 1:8፥ 4:15፥ 1ኛ ጴጥ 2:2፥

### 3.2.3 እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል የሆነ የሚሰገድለትና የሚከበር ከአብ የወጣ በነቢትያት የተነገረ የሕይወት ጌታና ሰጪ እንደሆነ መንፈሳዊ ምላተ አካል ያለውና መለኮት መሆኑን ዓለምን ስለኃጢያት ስለ ፅድቅና ስለፍርድ እንደሚወቅስ በምዕመናን ውስጥ አድሮ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራቸው እንደሚያስተምራቸው እንደሚያፅናናቸው የቅድስና ኑሮ ለመኖር እንደሚያስችላቸው ለአገልግሎትም ኃይልና የፀጋ ስጦታዎችን እንደሚሰጣቸው ታምናልች። ዘፍ 1:23፥ ማቴ 3:16፥ 10:20፥ ዮሐ 14:16-17፥ 26፥ 15:26፥ 16:7፥8፥13፥ 17:8፥ የሐዋ 1:8፥ 5:3-4፥ 1ኛ ቆሮ 3:16፥ 12:4-11፥ ገላ 4:6፥ 2ኛ ጴጥ 1:21፥

3.2.4 የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና ሙላት

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምነው የዳኑ ምዕመናን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋሪያት ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የሰጠውን ተስፋ ዛሬም ሊቀበሉ እንደሚችሉ የመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታዎችም በቤተክርስቲያን እንደሚሰሩ

ታምናለች፥ ታስተምራለች ሙላቱንም እንዲያገኙ ትፀልያልች። ኢዮኤል 2:28-29፥ማቴ 3:11፣ የሐዋ 1:8፥ 2:1-4፥ ሮመ 12:3-8፥ 8:14-18፥ 10:44-48፥ 19:1-9፥ 1ኛ ቆሮ 12:1-31፥ 14:1-40፥

3.3 .1 ቅዱሳን መላእክት፣

ቅዱሳን መላእክት የራሳቸው ስብዕና (Person) ያላቸው በመንፈሳዊ አካል የሚገኙና በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ንፁህ የሆኑ መንፈሳዊ ሠራዊት ሲሆኑ ለዘላለም የማይሞቱ ፍጡራን ናቸው። ዕውቀታቸው፥ ብርታታቸው ከሰው የሚበልጥ የስልጣን ተዋረድ ያላቸውና በመካከላቸውም በፆታ የተከፋፈለ መደብ የሌላቸው በእግዚአብሔር ፊት ሆነው ፈቃዱን በማድረግ እግዚአብሔርን ዘወትር በአክብሮት በውዳሴ በምስጋናና በስግደት የሚያገለግሉ የሚታዘዙ ጌታ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ የሚያጅቡት መሆናቸውን ታምናለች። ዘፍ 21:1፥ መሳ 13:15-16፥ 2ኛ ሳሙ
24:16፥ 1ኛ ነገ 19:5፥ 7፥ 2ኛ ነገ 19:35፥1ኛ ዜና 21:15 2ኛ ዜና 32:21፥ መዝ 8:5፥ 103፡ 20-21፥ ኢሳ 37፡36፥ዳን 3:28፥ 6:22፥ 10:13፥ ማቴ 18:10፥ 13:41፥ 22:30፥ 26:50፥ ማር 8:38፥ 13:32፥ ሉቃ 20:36፥ 22:43፥ ዮሐ 20:12፥ የሐዋ ሥራ 12:23፥ 27:23፥ 27:23 1ኛ ቆሮ 6:3፥ ቆላ 1:16፥ ዕብ 1:14፥ ይሁዳ 9፥ ራዕይ 22:8።

3.3.2

ሰው በእግዚአብሄር እና በእግዚያብሄር አምሳል እንደተፈጠረና በሃጢያቱ ምክንያት ከእግዚአብሄር እንደተለየና እንደወደቀ ታምናለች። ሃጢያቱም ከእግዚአብሄር ለይቶ በስጋው ሞትን እንዲሁም በመንፈዉ ላይ የዘላለምን ሞት እንዳመጣበት ታምናለች። ሃጢያት የሌለበት ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ለሃጢያቱ መድሃኔት እንደሆነም ታምናለች።ዘፍ 6:5,2:17,6:5፣ኤር 17:9፣መዝ 14:1-3፣ ዩሃ 3:6,5:40፥ 6:53፣ሮሜ 3:10-19፣ኤፌ 2:1-3,1ጢሞ 5:6,1ዮሃ 3:8

3.4 ሰይጣን

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ጥበበኛና ውብ አድርጎ ፈጥሮት ፍጹምና ፈጣሪውን የሚያገለግል ታላቅ መላክ እንደነበረ ሆኖም እንደ እግዚአብሔር ታላቅ ለመሆን በነበረው ምኞት ሌሎችን መላእክት እንዳሳተና እንደወደቀ በእባብ ተመስሎ የመጀመሪያዎቹን ሰዎች እግዚአብሔር ላይ እንዲያምጹ እንዳታለለ በባህርይው የረከሰ ሃሰተኛ የኃጢያትና የጥፋት ሁሉ ምንጭ የእግዚአብሔርና የሰው ጠላት የጨለማ ዓለም ገዥ እንደሆነ በመጨረሻም ከተከታዮቹ ጋር ወደተዘጋጀለት እሳት ባህር እንደሚጣል ታምናለች፥ ታስተምራለች። ዘፍ 3:1-6፥ ኢሳ 14:12-15፥
ሕዝ 28:12-19፥ ማቴ 25:41፥ ማር 1:27 ዮሐ 5:19፥ 8:44፥ ኤፌ 6:12« 1ኛ ጴጥ 5:8፥ 1ኛ ዮሐ 5:19 ራዕይ 12፡ 3-4፥ 7-9፥ 20:10

3.5 ድነት

ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት በመስቀል ላይ በመሞት ራሱን ቤዛ አድርጎ በሰጠው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ሰው በእግዚአብሔር ጸጋ እንደሚድን ታምናለች። ይህም ሰው ስለ ኃጢአቱ ተጸጽቶ ንስሃ በመግባት በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ተወልዶም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚሆንና በክርስቶስም መንፈሳዊ ባርኮትንና የዘላለም ሕይወትን እንደሚሰጠው ታምናለች። ኢሳ 53:4-12 ዮሐ 1:12-13፤ 3:3-18፥የሐዋ ሥራ 13:38-39፥ 4:12፥ ሮሜ 3:20-26፥ ኤፌ 1:3-14፥ 2:8-9፥ ዕብ 9:25-28፤

3.6 አለኝታ

ምዕመናን ከሞት ወደ ሕይወት መሸጋገራቸውን ለማወቅ እንደሚችሉና እግዚአብሔርም ከመውደቅ ሊጠብቃቸው እንደሚችል ይሁን እንጂ በጸጋ ለማደግና ከጌታ ላለመለየት ደህንነታቸውን ለመጠበቅ በዕምነት የመታዘዝ ኃላፊነት እንዳለባቸው ታምናለች። ዮሐ 5:24፥ ሮሜ 11:17-22፥ 1ኛ ቆሮ 10:1-3፥ ዕብ 3:12-19፥ 1ኛዮሐ 5:13

3.7 ቤተክርስቲያን

3.7.1. የቤተክርስቲያን መሠረትና መሥራች ራስና መሪ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ታምናለች፥ ታስተምራለች።

3.7.2 ቤተክርስቲያን ክርስቶስን በማመን ንስሃ ገብተው ዳግመኛ የተወለዱና መንፈስ ቅዱስም አንድ አካል ያደረጋቸው ምዕመናን ሁሉ ያሉባት የክርስቶስ አካል መሆንዋንና ለክርስቶስ ቃል መታዘዝ እንዳለባት ታምናለች። የሐዋ ሥራ 16:31፥ 1ኛ ቆሮ 12:12-17፥ ገላ 3:26፥ ኤፌ 1:22-23፥ 2:22፥ 5:23-26፥ 1ኛ ጴጥ 2:9-10፤

3.8 ትንሣኤ ሙታን

ኢየሱስ ክርስቶስ የማይሞትና የማይበሰብስ አካል ለብሶ ከሙታን እንደተነሳ እንዲሁም ጻድቃንና ኃጥአን በማይሞትና በማይበሰብስ አካል ከሙታን ተነስተው ጻድቃን ወደ ዘላለም ደስታ ኃጥአን ግን ወደ ዘላለም ስቃይ እንደሚሄዱ ታምናለች፥ ታስተምራለች። ዳን 12:2፤ ዮሐ 5:28-29፥ 20:24-29፥ 1ኛ ቆሮ 15:20-23፥ 42-44፥ 51-54፤ 3.9 የሰው ውድቀት

እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክና አምሳል መልካም አድርጎ መፍጠሩን ሰውም በሰይጣን ተታሎ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመጣሱ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሞቶ ኃጢያተኛ መሆኑን ከሥጋዊ ሞትና ከሰይጣን በታች መዋሉንና ከዚህም ውድቀት ራሱን ለማዳን አለመቻሉን ታምናለች፥ ታስተምራለች። ዘፍ 1:26-27፥ 2:7፥ 16፥17፥ 3:1-22፥ ዮሐ 8:44፥ ሮሜ 5:6-8 ኤፌ 2:2-3፥ 12። እንደዚሁም ሰው ከፍጥረቱ ኃጢዓትን ይዞ የሚወለድ እንደሆነ ታምናለች፥ ታስተምራለች። መዝ 51:5

## 3.9 የቤተክርስቲያን ሥልጣንና ሃላፊነት

በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጌታ ኢይሱስ ለቤተክርስቲያን ከዚህ የሚከተሉትን እንድታከናውን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደሰጣት ታምናለች፡-

3.10 የክርስቶስን ወንጌል በመስበክ ሰዎች በእርሱ ካመኑ በኋላ አስተምራ የቅዱስ ጥምቀት ሥርዓት በመፈጸም ደቀ መዝሙር ታደርጋለች። ማቴ 28:19-20፥ ማር 16፡ 15-16፥ የሐ ሥራ 2:37-42

3.10.2.1 በእግዚአብሔር መንፈስ እየተመራች አገልጋዮቿን መርጣ መሾም። የሐ ሥራ 6:1-6፥ 13:1፥ 14:23፥ 20:28፥ 1ኛ ጢሞ 3:1-13

3.10.2.2 ማንኛውም አገልግሎት አካሉን ማለትም ቤተክርስቲያንን ለማነጽ የተሰጠና ተጠሪነቱም ለቤተ ክርስቲያን መሆን እንዳለበት ታምናለች። 1ኛ ቆሮ 12:4-31

3.10.3 አማኞችን ማስተማር መምከር መገሰጽና የማይታዘዙትን ንስሃ ገብተው ሕይወታቸውን እንዲያስተካክሉ መርዳት የቤተክርስቲያንን ምስክርነትና መንፈሳዊ ጤንነት ለመጠበቅ እንዲሁም መንፈሳዊ ኑሮን እንዲኖሩ በሥርዓት ለመምራት እንዲቻል አመጸኞችን ከቅዱሳን ሕብረት ማግለል። ማቴ 18:15-18፥ 28:19-20፥ 1ኛ ቆሮ 5:1-13፥ 2ኛ ቆሮ 2:5-11፥ ገላ 6:1-2፥ 1ኛ ተሰ 5:12-14፥ 2ኛ ጢሞ 4:2፤

3.10.4 ከጌታ የተቀበለችውን አደራ አላማዋ አድርጋ እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት ለእውነትና ለፍትህ መቆም። ኢሳ 1:16-17፥ ሉቃስ 3:19-20

3.10.5 በቸር ሥራ አገልግሎት መትጋት። ማቴ 25:35-40፥ 2ኛ ቆሮ 8ና9፥ ያዕቆብ 2፡14-17፥

3:11 ቅዱሳን ሚስጥራትና የክርስትና ሥርዓቶችን ማከናወን:-

ሀ/ ቅዱሳት ሚስጥራት

ቅዱሳት ሚስጥራት የሚባሉት በሚታይና በሚጨበጥ መንገድ የማይታየውን መንፈሳዊ ሚሥጥርን የሚገልጡ ጌታ ኢየሱስ በዚህ ሳለ የፈጸማቸውን እንድንፈጽማቸው ያዘዘንን በጌታ ኢየሱስ ሕይወት ውስጥ ትርጉምና መንፈሳዊ ሚሥጥራን ያዘሉና ብናደርጋቸውም በረከትን የሚያስገኙ መሆናቸውን ታስተምራለች። እነዚህም:-

3.11.1 ቅዱስ ጥምቀት

ጥምቀተ ንስሃ ገብቶ ኢየሱስን በእምነት አዳኙና ጌታ አድርጎ በመቀበል ከዳነ በኋላ በአብ በውልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በውኃ ውስጥ በማጥለቅ የሚከናወን ቅዱስ ሥራርዓት መሆኑን ታምናለች። ማቴ 28:19-20፥ የሐዋ ሥራ 2:37-41፥ 16:30-34፥ ሮሜ 6:1-8፥ ቆላ 2:12፣

3.11.2 የጌታ እራት

የጌታ እራት የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ስለሰው ልጆች ኃጢያት መቆረሱንና ደሙ ስለኃጢያት ሥርየት መፍሰሱን የሚያመለክት በሕብስትና በጽዋ የሚከናወን የጌታ ሞት መታሰቢያ ሲሆን መሳተፍ የሚገባቸው ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው ተቀብለው የውሃ ጥምቀት ሥርዓት የፈጸሙ በቅድስናና በሥርዓት ለመመላለስ የወሰኑና ህይወታቸውንም በየዕለቱ በንስሃ በማደስ የሚተጉ ምዕመናን ብቻ መሆኑን ታምናለች። ማቴ 26:26-28፥ የሐዋ ሥራ 2:42፥ 1ኛ ቆሮ 10:16-17፥ 11:17-34፤ በተጨማሪም የእግር መተጣጠብ ስነ ስርአት ዮሃ.13፤ 1-17፣ማቲ2 6:14:14-39

ለ/ የክርስትና ሥርዓቶች 3.11.3

3.11.3 ለህሙማን ስለ መጸለይ

ሕሙማን በጸሎት ሊፈወሱ እንደሚችሉ ታምናለች። የእምነት ጸሎትም ታደርጋለች። ማር 16:17-18፥ 3ኛ ዮሐ ቁ2፥ ያዕ 5:24-26

3.11.3.1 የእግር መተጣጠብ ስር አት;ዩሃንስ 13:1-17፣ማቲ 26:14-39

3.11.4 *ጋብቻ*

*ጋብቻ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ብቻ የሚፈጸም እግዚአብሔር የመሠረተው፣ የቀደሰውና የሁለት ምዕመናን አንድነት ኪዳኑን ሞት ብቻ የሚያፈርሰው እንዲሁም ቤተክርስቲያን ልትንከባከበው ልትጠብቀው የሚገባ ቅዱስ ሥርዓት መሆኑን ታምናለች፥ ታስተምራለች። ዘፍ 2:18-25፥ ሮሜ 7:1-13፥ 1ኛ ቆሮ 7:10-16፥ 39፣ ኤፌ 5:23-33፥ ዕብ 13:4፤ እድሜያችው ለጋብቻ የደረሰ ሁለት ወንድና ሴት ቢያንስ 18 አመት ሊሆናቸው እንደሚገባና ሁለቱም ተላላፊ ከሆነው የአባለዘር በሽታ(STD) ምርመራ ውጤታቸውን ለቤተ ክርስትያን ማቅረብ ይኖርባቸዋል።*

*ጋብቻ ነክ መመሪያ*

3.11.4.1 ክርስቲያናዊ ጋብቻ የሚያምን ከሚያምን ጋር እንጂ የሚያምን ከማያምን ጋር ፈጽሞ መጋባት እንደሌለበት መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚያስተምር ቤተክርስቲያን አትቀበለውም፤ ይህንንም በተመለከተ ከቤተክርስቲያኒቱ ውሳኔ ጋር አገልጋዮች ወይም አባላት መቆም ይገባቸዋል። አማኙ ወገን ግን እምቢ ብሎ ካላመነው ወገን ጋር ጋብቻ ቢፈጽም ቤተክርስቲያኒቱ በአማኙ ዓባል ላይ ተገቢውን የዲስፕሊን እርምጃ ትወስዳለች። 2ኛ ቆሮ 6:14-16

3.11.4.2 ሁለት የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ወደ ትዳር ኃሳብ ከመድረሳቸው በፊት ኃሳባቸውን ለቤተክርስቲያኒቱ እረኛ በመግለጽ በእጮኝነት ከ 3-6 ወር እንዲቆዩ ይደረጋል።

3.11.4.3 የቤተክርስቲያኒቱ እረኛ ሁለቱን ወገኖች በጸሎት፥ በምክርና የጋብቻን ትምህርት በመስጠት ተገቢውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ይረዳል።

3.11.4.4 አንድ የቤተክርስቲያን አባል የሆነ ማንኛውም አማኝ በመሠረታዊ እምነት ከምትመሳሰል ቤተክርስቲያን አባል ጋር ለመጋባት ቢወስን የቤተክርስቲያን መሪዎች ትጭጭቱን የሚያጸድቁት ሲጋቡ ወደ አንዳቸው ቤተክርስቲያን እንደሚጠቃለሉ ከሆነ ነው። ይህም ለተጋቢዎቹ ጤናማ ትዳርና ለቤተክርስቲያን ደህንነት ሲባል ነው።

3.11.4.5 የእግዚአብሔር ፈቃድ አለመሆኑን እያወቀ ከማያምን ሰው ጋር የሚጋባ የቤተክርስቲያን አባል የጋብቻን ሥነሥርዓት ክቡርነት ስለሚያበላሽ ምሳሌነቱም ለሌሎች የልብ ድፍረት ሰጥቶ እንዲስቱ ስለሚያደፋፍር ቤተክርስቲያን እንዲህ አይነቱን ጋብቻ አትደግፍም። በዚህ ምክንያት ቢያንስ ለ አንድ አመት በቤተክርስቲያን ከሚሰጡ ሥርዓቶችና አገልግሎት እንዲለይ ይደረጋል፤በተጨማሪም በየጊዜው በህየወቱ የሚታየው ለውጥ ከእረኛው ለሽማግሌዎች ጉባኤ ሪፖርት የደረጋል።አማኝ ግለሰቡንም ቤተክርስቲያን የፍቅር እጆቿን በመዘርጋት ወደ ትክክለኛው ክርስቲያናዊ ኑሮ በንስሐ እንዲመለስ ትረዳዋለች። ከዚያም የንስሐው ፍሬው ታይቶ የአባልነት መብቱ እንዲታደስ ሲደረግ የማያምነው ክፍል ግን ወደ ጌታ እስኪመጣ ድርስ በቤተክርስቲያን ሽማግሌነትና በዲያቆንነት አያገለግልም።

3.11.4.6 ጌታን ከማወቃቸው በፊት ተጋብተው የነበሩ ወገኖች ጌታን ቢቀበሉና በቤተክርስቲያን የቃል ኪዳን ሥነስርዓት እንዲደረግላቸው ቢጠይቁ ቤተክርስቲያን ለአዲስ ተጋበዎች የሚደረገውን የጋብቻ ሥነሥርዓት አታስፈጽምላቸውም። ቤተክርስቲያንም በዝግጅታቸው ላይ በመገኘት ለትዳራቸው ጸሎትና ቡራኬ ልታደርጋላቸው ትችላለች።

3.11.4.7 የቤተክርስቲያን አባላት የሆኑ ሁለት ተቃራኒ ፆታዎች ከጋብቻ በፊት በአንድ ላይ መኖራቸው እግዚአብሔር የቀደሰውን ጋብቻ የሚያረክስ በመሆኑ ቤተክርስቲያን እንዲህ አይነቱን ሁኔታ አጥብቃ ትቃወማለች። በተጨማሪም ከጋብቻ በፊት የሚደረገውን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሞ የማትደግፍ በመሆኗ ለእንደዚህ አይነቶቹ ሰዎች የጋብቻ ቃል ኪዳን አታደርግላቸውም። ቤተክርስቲያንም ተገቢውን የዲስፕሊን እርማጃ በአንቀጽ 11.19 እና 11.20 መሠረት ትወስዳለች።

3.11.4.8 በጋብቻ አንድነት የተሳሰሩ አማኞች አንደኛው ወገን በዝሙት ኃጢአት ቢወድቅ በታማኝነት የቆየው ወገን የመለየት መብቱን እንደ እግዚአብሔር ቃል የተጠበቀ ቢሆንም ቤተክርስቲያን የይቅርታ መንፈስ እንዲሰፍን የበኩሏን ጥረት ከማድረግ በስተቀር መለየትን አታደፋፍርም።

3.11.4.8.1 ታማኝ ያልሆነው ወገን ልባዊ ንስሃ ቢያደርግና የተበደለው ግን ሊቀበለው ፈቃደኛ ካልሆን መለየቱ የተጠበቀ ይሆናል። ታማኝ ባልሆነው ወገን ላይም ቤተክርስቲያን የዲስፕሊን እርምጃ ትወስዳለች። ንስሃ ከገባም ተሃድሶ ታደርግለታለች።

3.11.4.8.2 በዝሙት ምክንያት ትዳራቸው የፈረሰ ወገኖች መፋታታቸውን በተመለከተ ከመንግሥት አካል ጸድቆ በቤተክርስቲያንም ከታመነበት በኋላ የቃል ኪዳኑን ሕብረት ያላፈረሰው ወገን የትዳር ህይወት መስርቶ ሊኖር ይችላል።

3.11.5. ልጆችን ለጌታ ማስረከብ

ልጆችን ለጌታ አደራ መስጠት በብሉይ ኪዳን ከእግዚአብሔር ለሕዝበ እሥራኤል ተሰጥቶ በአዲስ ኪዳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ እርሱም ራሱ በአገልግሎቱ ጊዜ በተግባር ሲገልጸው የነበረ ነው። ቤተክርስቲያንም ይህን ሥርዓት የምታከናውነው ከአማኝ ወላጅ የተወለዱትን ሕጻናት ለእግዚአብሔር ባርኮትና ጥበቃ ለጌታ አሳልፈን የምንሰጥበት፥ ወላጆችም እግዚአብሔርን በማመስገን በጌታ መንገድና ሥርዓት ህጻናት ልጆቻቸውን

ለማሳደግ ቃል የሚገቡበት መሆኑን ታምናለች፥ ይህም የሚከናወነው ቤተክርስቲያኒቱ ባላት የሥርዓት ማስፈጸሚያ ደንብ መሠረት ይሆናል። 1ኛ ሳሙ 1:28፥ ማር 10:13-16

3.12 ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

3.12.1 ማንኛውም ክርስቲያን፡-

ሀ) ከሁሉም በላይ በቅድሚያ እግዚአብሔርን መፍራት ማፍቀር መታዘዝና ማክበር እንደሚገባው ታምናለች ታስተምራልች። ምሳሌ 1:7፥ማቴ 22:7፥ የሐዋ ሥራ 4:18-20፥ 5:29

ለ) እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት ለአገር መሪዎች በታማኝነትና በቅንነት መታዘዝ ማክበር የሚፈለግበትንም ግብር መክፈልና ለእነርሱም መጸለይ እንደሚገባ ታምናለች፥ ታስተምራለችም። ሮሜ 13:1-7፥ 1ኛ ጢሞ 2:1-4

ሐ) በተቻለ መጠን ከሰው ጋር በሰላምና በፍቅር መኖር እንዳለበት ታምናለች፥ ታስተምራለችም። ዘሌ 19:17-18፥ ሮሜ 12:14-21፤

መ) ቤተክርስቲያንና የቤተክርስቲያን መሪዎችን (አገልጋዮችን) እንደ እግዚአብሔር ቃል መሰረት ሊያከብራቸው ሊያፈቅራቸው ሊታዘዛቸው እንደሚገባ ታምናለች፥ ታስተምራልችም። 1ኛ ተሰ 5:12-13፥ ዕብ 13፥17

3.12.3 ክርስቲያን ለዓለም ክብርና ጥቅም ሳይሸነፍ በኑሮውና ከእግዚአብሔር በተሰጠው ማንኛውም ነገር ባለአደራነቱን ሳይዘነጋ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስቀደም እንደሚገባው ታምናለች፥ ታስተምራለችም፤ ምሳሌ 3:9-10፥ ሚል 3:7-12፥ ሉቃስ 12:35-48፥ ሮሜ 12:1-2፥ 1ኛ ዮሐ 2:1-6፥ 15-17፤

3.12.3 መለየት

ምዕመናን ከዓለማዊነትና ለዓለም ከሚመቹ ከንቱ ነገሮች ተለይተው ለእግዚአብሔር ክብር በኢየሱስ ክርስቶስ የጽድቅ ኑኖ መኖር እንደሚገባቸው ታምናለች። ዘዳ 22:5፥ ዮሐ 17:15፥ ሮሜ 12:1-2፥ 2ኛ ቆሮ 6:14-18፥ 1ኛጢሞ 1:8-10፥ 2:9-10፥ ቲቶ 2:11-14፥ 1ኛ ጴጥ 3:1-6፥ 1ኛ ዮሐ 2:15-16፤

3.13 የመጨረሻ ነገሮች

3.13.1 ገነትና ሲዖል (የመጠባበቂያ ስፍራ)

በሥጋ ሞትና በትንሳኤ መካከል ባለው ጊዜ ጻድቃን (በእምነት የእግዚአብሔር የሆኑት) ከክርስቶስ ጋር በገነት በደስታ፥ ኃጥአን ግን በሲዖል ስቃይ እንደሚኖሩ ታምናለች። ሉቃስ 16:19-31፥ 23:43፥ የሐዋ ሥራ 2:27፥ 2ኛ ቆሮ 5:6-8፥ ፊልጵ 1:21-23፥ 2ኛ ጴጥ 2:9፤

3.13.2 የክርስቶስ ዳግም ምጽአት

የምዕመናን ሁሉ ተስፋ መሆኑን በምፃቱም ጊዜ በክረስቶስ የሞቱ ቅዱሳን አስቀድመው የማይበሰብሱ ሆነው ከሙታን እንደሚነሱ በሥጋ በህይወት ያሉ ምዕምናን ተለውጠው ከእነርሱ ጋር ጌታን በአየር ለመቀበል እንደሚነጠቁና በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ብድራታቸውን ለመቀበል እንደሚቀርቡ ታምናልች። ማቴ 25:1-30፥ ሉቃስ 17:4-37፥ ዮሐ 14:1-3፥ 18፥ የሐዋ ሥራ 1:11፥ ሮመ 14:10-12፥1ኛ ቆሮ 3:10-15፥ 15:51-52፥ 2ኛ ቆሮ 5:6-10፥ 11:2፥ 1ኛ ተሰ 4:15-17፥ ቲቶ 2:12-13፥ ራዕይ 19:7-9፤

3.13.3 ሀሰተኛው ክርስቶስ በሰይጣን ሃይልና ሥልጣን ምድርን የሚገዛ የክርስቶስ ተቃዋሚ እንደሆነ እርሱም ዓለምን ሲገዛ በምድር ላይ ታላቅ የመከራ ጊዜ እንደሚሆን የእሥራኤል ሕዝብ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በመሲህነቱ ለመቀበል እድል የሚያገኙበት ገዜ እንደሚሆን ቤተክርስቲያን ታምናለች። ዳን 9:27፥ 11:31፥ ዘካ 12:14፥ ማቴ 24:15-22፥ 1ኛ ተሰ 4:13-17፥ 2ኛ ተሰ 2:1-12፥ ራዕይ 13:1-18፤

3.13.4 የኢየሱስ ክርስቶስ ለሺህ ዓመት በምድር ላይ መንገሥ

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር መጥቶ ለሺህ ዓመት በጽድቅ እንደሚገዛ በጌታ ሕያዋን የሆኑ ቅዱሳን በመንግሥቱ ተካፋይ እንደሚሆኑ ታምናለች። ኢሣ 11:1-16፥ ራዕይ 19:11፥20:1-6፥

3.13.5 የእሳት ባህር

የእሳት ባህር በሕይወት መጽሐፍ ተጽፈው ያልተገኙት ሰዎች ዲያብሎስና ተከታዮቹ ለዘላለም የሚሰቃዩበት የቅጣት ሥፍራ እንደሚሆን ታምናልች። ማቴ 25:42፥ ማር 9:42-48 ራዕይ 20:7-15፥ 21:8፥ ይሁዳ 1፥13-15፤

3.13.6 መንግሥተ ሰማያት

መንግሥተ ሰማያት በጌታ ኢየሱስ አምነው ድነትን ያገኙ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም በደስታ የሚኖሩባት ስፍራ መሆኗን ታምናለች። ማቴ 25:34፥ ራዕይ 21:1-7፥ 22:1-5

## አንቀጽ 4

## ዓላማ

4.1 ሰዎች ከኃጢዓት፣ ከሰይጣንና ከዘላለም ፍርድ ክርስቶስን በማመን አምልጠው በኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ፤ ዮሐ 3:16፥ ሐዋ 26፡ 17 እና 18፥ ይህን ለማከናወን፡-

4.1.1 ተግባር፡

4.1.1.1 የእግዚአብሔርን ቃል በስልጣን በሙላትና በግልጽነት መስበክና ማስተማር። ማር 16፥20

4.1.1.2 ወደዘላለም ጥፋት የሚሄዱትን ሰዎች ሁሉ ለመታደግ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግስትና ወደዘላለም ሕይወት መመለስ። ዮሐ 3፥16፤

4.1.1.3 የቤተክርስቲያኒቱን ምዕመናን በክርስትና እምነታቸው እንዲያድጉ እንዲጠነክሩና ደቀመዝሙር በማድረግም የወንጌል መልዕክት ላልደረሳቸው የታላቁን ተልዕኮ ዓላማ እንዲያካሂዱ ማደፋፈርና ማበረታታት። ማቴ 28፥18-20

4.1.1.4 በቤተክርስቲያን ውስጥ በአካባቢዋና እንዲሁም በዓለም ዙሪያ አቅሟ እንደፈቀደ መጠን ወንጌልን ማሰራጨትና ለተቸገሩ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እርዳታ መድረስ።

4.1.1.5 ለሰዎች ሁሉ ለመንግሥት ባለሥልጣኖችም ወደእግዚአብሔር ጸሎት ምልጃና ምስጋና ማቅረብ። 1ኛ ጢሞ 2፥1-2

4.1.1.6 አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ማቋቋምና ማደራጀት። ቲቶ 1፥5

4.1.1.7 ቤተክርስቲያን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለችውን በማቴ 28:18 የተገለጸውን ታላቁን ተልዕኮ ተግባራዊ ማድረግ፤

4.1.1.8 ለወንጌል ሥራ የምታሠማራቸውን አገልጋዮች አቅሟ በሚፈቅደው ሁሉ መደገፍ፤

4.1.1.9 መሰረታዊ የክርስትና እምነትንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን አበክሮ ማስተማርና ማጽናት፤

4.1.2 ስልጣን

4.1.2.1 ዓላማውን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑትን ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች የመግዛት የመሸጥ የመለወጥና የማስተላለፍ በባለቤትነትም የመያዝና የማስተዳደር፥

4.1.2.2 በአንቀጽ 4.1.2.1 ተመዝግበው የተያዙትን የቤተክርስቲያኒቱን ንብረቶች በቦርድ የበላይ ጠባቂነት ከቦርዱ በተመረጡ አባላት የመያዝ፥

4.1.2.3 ስጦታዎችን፣ ውርሶችን፣ ንብረቶችንና ሌሎችንም ዓላማዋን ለማስፈጸም የሚረዱ ቁሳቁሶችን በልግስና ተቀብላ የማስተዳድር፥

4.1.2.4 በቤተክርስቲያኒቱ ስም ገንዘብ የመበደር፥ የብድር ውሎችን የመግባትና ውሎችንም የመፈረም፥ ሞርጌጆችን ለመግዛት ሲታሰብ በሽማግሌዎች ቦርድ አማካይነት በሚቀርበው ሃሳብ ላይ ተወያይቶ በድምጽ ብልጫ የመወሰን፥

4.1.2.5 የቤተክርስቲያኒቱ የዓመት ዕቅድና በጀት በሽማግሌዎች ቦርድ በሚቀርበው ዝርዝር ሃሳብ ላይ ተነጋግሮ በድምጽ ብልጫ በማጽደቅ፥ ይህንኑ በተግባር ለመተርጎም አስፍላጊውን ተሳትፎ ሁሉ የማድረግ፥

4.1.2.6 በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 11 መሰረት በሽማግሌዎች ቦርድ በሚቀርበው እጩ እረኛ ላይ ድምጽ በመስጠት የመምረጥ፥

4.1.2.7 በዓመት ሁለት ጊዜ በሚደረገው መደበኝ የአባላት ስብሰባ ላይ በመገኘት በሚቀርበው ሪፖርት ላይ ገንቢ ሃሳብና አስተያየት መቀበል፥

4.1.2.8 በቤተክርስቲያን ለሚወሰዱ ሥነ ሥርዓታዊ እርምጃዎች ተግባራዊነት አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ የማድረግ፥

4.1.2.9 የመተዳደሪያ ደንቡ መሻሻል በሚያስፈልገው ጊዜ መሻሻል በሚያስፈልገው አንቀጽ ላይ ተገቢውን የማሻሻያ ሃሳብ የመስጠትና ተስተካክሎ የሚቀርበውንም ለአባላቱ በማቅረብ ማስጸደቅ፥

4.1.2.10 አትራፊ ድርጅት ባለመሆኗ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ዓላማዋን ለማስፈጸም በተለያዩ መንገዶች የገንዘብም ሆነ የማቴሪያል ዕርዳታ ከለጋሾች የማሰባሰብ (ፈንድ ሬይዚንግ) ዘዴዎችንና ዕቅዶችን በማውጣት ተግባራዊ በማድረግ፥

4.1.2.11 የቤተክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎችና መጋቢዎች እንዲሁም ማንኛውም አገልጋይና አባል ለቤተርስቲያን ሥልጣን ላለመገዛት፦

-የእንቢተኝነት መንፈስ የሚያሳይ

-የስህተት ትምህርትን ተቀብሎ የሚያስተላልፍ

-በምዕመኑም መካከል ሆነ በውጭ ግልጽ የሆነ ኃጢአት የፈጸመ ወይንም ሌላው ሲፈጽም ተባባሪ ሆኖ ሲገኝ እንደ ሁኔታው ማስተማር መምከርና መገሰጽ፣ ከአገልግሎት፣ ከስልጣንም ሆነ ከአባልነት ለተወሰነ ጊዜ ወይም ፈጽሞ የማገድ፥

## አንቀጽ 5

## ወገናዊነት የማይንጸባረቅባቸው እንቅስቃሰዎች

ይህ ድርጅት በሳናንቶኒዮ ትርፍ አልባ የሃይማኖት ድርጅቶች ህግ መሰረት ከላይ የተጠቀሱትን ሃይማኖታዊ ተልዕኮዎችን ለማራመድ የተመሰረተ ስለሆነ ለትርፍ የማይሮጥና በገለልተኝንት ከማንኛውም ፓርቲ ወይንም የፖለቲካ ድርጅት ተጸኖ ነጻ የሆነ ድርጅት ነው። ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት በጉልህ የሚታይ የድርጅቱ እንቅስቃሴና ህልውና ህግን ለመጋፋት ወይም ለማዛነፍ ሲባል ጽሁፎችን አያትምም አያሰራጭምም፥ መንግስታዊ

ቢሮን ለመያዝ ለሚወዳደር ለመንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት ድጋፍ ለመስጠት ወይም ላለመስጠት በማንኛውም የፖለቲካ ቅስቀሳ አይካፈልም።

## አንቀጽ 6

### ቤተክርስቲያንና ግንኙነቶች

6.1 ቤተክርስቲያን

ቤተክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ተዋጅተው የክርስቶስ አካል ብልቶች የሆኑ ምዕመናን ስብስብ ስትሆን በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ተመስርታ የምስራቹን ቃል በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ሥልጣን የምታውጅ የገሃነም ደጆች የማይቋቋሟት ለክርስቶስ የታጨች በመጨረሻም የምትነጠቅ ሙሽራ ናት። ማቴ 16:18፥ የሐዋ ሥራ 20:28 1ኛ ጴጥ 1:19፥ 1ቆሮ 12:27፥ ኤፌ 5:20፥ የሐዋ ሥራ 14:27፥ ኤፌ 2:20 ማር 16:15፥ ማቴ 28:18-20፥ የሐዋ ሥራ 4:31-33፥ 1:18፥ 2ኛ ቆሮ 11:2፥ ኤፌ 5:27፥ ራዕ 19:7፥ 1ኛ ተሰ 4:13-18፥

በሳናንቶኒዮ የኢትዮጲያንና የኤርትራውያን ቤተ ክርስትያን   ክርስትያኖች ህብረት

ከላይ ስለ ቤተክርስቲያን በተሰጠው ትርጉም መሰረት የክርስቶስ አካል የሆነች አጥቢያ ቤተክርስቲያን ናት። በሳናንቶኒዮ የኢትዮጲያንና የኤርትራውያን ቤተ ክርስትያን   ክርስትያኖች ህብረት

6.2.1 ግንኙነቶች

6.2.2 ቤተክርስቲያኒቱ ነጻና ራስ ገዝ እንደመሆኗ መጠን ማንኛውም ግለሰብ፥ ድርጅት ሆነ ተቋም በህልውናዋ በዓላማዋና በአሰራሯ ጣልቃ መግባት ፈጽሞ አይችልም። ቤተክርስቲያኒቱ አዘጋጅታ ከምታወጣቸው የጹሁፍ የኦዲዮና ቪዲዮ የቅጂ ቁሳቁሶች በቀር ማንኛወም ሌላ ግለሰብ፥ ድርጅት ሆነ ተቋም የራሱን የጽሁፍና የቅጂ ቁሳቁሶች ማሰራጫ አድርጎ መጠቀም አይችልም። በድርጅቱ በኩል የሚሰራጩትን ምንም አይነት መንፈሳዊ ጹሁፎች ኦዲዮና ቪዲዮዎች እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁሶች ምንጫቸውን ቤተክርስቲያን የምታውቃቸውን ከተላኩበትም ቤተክርስቲያን ወይም ሚኒስትሪ በአባሪ ደብዳቤ መላክ ይኖርባቸዋል። በአንጻሩ ቤተክርስቲያኒቱ እንደሁኔታውና በንጽህና ማንኛውንም አይነት የገንዘብም ሆነ የጥሬ እቃዎች እርዳታና ስጦታ የቤተክርስቲያኒቱን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያስችል ከማንኛውም ግለሰብ ሆነ ድርጅት ከመቀበል አትታገድም። በጽድቅ ያልመጣ የሆነን ሳታውቅ በትቀበል እንኳን ትመልሳለች።

6.2.3 ይህች ቤተክርስቲያን በዕምነቷ ለሚመሳሰሏትና መንፈሳዊ አንድነትን ከሚጠብቁ ወንገላዊያን አብያተ ክርስቲያናትና መንፈሳዊ ድርጅቶች ጋር ለወንጌል አገልግሎት ሕብረትና ግንኙነት ታደርጋለች።

6.3 የድርጅቱ ንብረት አያያዝ

ሀ) የድርጅቱ ንብረቶች በሙሉ በንብረት ኃላፊው አማካይነት ተመዝግበው ለቤተክርስቲያኒቱ አገልግሎት ብቻ ይውላሉ

ለ) ይህ ትርፍ አልባ ድርጅት የወንገል ሥራውን ፈጽሞ ያቆማል ብለን ባናምንም ይህ ሁኔታ ቢፈጠር በአሜሪካ በሃገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት (Internal Revenue) በኮድ ክፍል 501 (C) (3) መሠረት ያለው ንብረት በሙሉ ትርፍ አልባ ለሆነ መንፈሳዊ ድርጅት ይተላለፋል እንጂ ለአንድ የድርጅቱ አባል ለሆነ ግለሰብ አይተላለፍም።

## አንቀጽ 7

## አገልጋዮች

7.1 **የድርጅቱ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች** (Full Time Ministers)

የድርጅቱ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች መለኮታዊ ጥሪ ያላቸው እረኛ (ፓስተር) እንድ አስፈላጊነቱም ተባባሪ እረኛ (Associate Pastor) እና ረዳት መጋቢዎች እንዲሁም ወንጌላውያንና የወጣቶች መጋቢ (Youth Pastor) ይሆናሉ።

7.2 የአስተዳደር ሠራተኞች

ድርጅቱ አቅሙ እንድ ፈቀደ መጠን ቀጥሮ የሚያሰራቸው የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊና ፀሐፊ የመሳሰሉት ይኖሩታል።

7.3 በዚህ አገር አሠራር መሠረትም ቤተክርስቲያኒቱ አቅሟ እንደፈቀደ አስፈላጊውን ጥቅማ ጥቅሞች (Benefits) እንዲጠበቅላቸው ታደርጋለች። **ለዚህም ማስፈጸሚያ ያአስተዳደር manual ይዘጋጃል።**

## አንቀጽ 8

## የሽማግሌ ብቃት

8. 1 የቤተክርስቲያኒቱን መሠረተ ዕምነትና የመተዳደሪያ ደንብ የተቀበለ።

8.2 በእግዚአብሔርና በሰዎች ዘንድ መልካም ምስክርነት ያለው። 1ኛ ጠሞ 5:17፥ ቲቶ 1:6፤ 2:2

8.3 ቤተክርስቲያኒቱ የቆመችለትን አላማ የሚደግፍና የሚያራምድ። ፊል 2:22-24 ቆላ 4:12-13

8.4 ቀደም ሲል በቤተክርስቲያን አገልጎሎት ውስጥ ተሳትፎ የነበረው። የሐዋ ሥራ 14:20-23

8.5 ጊዜውን፥ ገንዘቡን፥ ጉልበቱንና እግዚአብሔር የሰጠውን ጥበብ በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ለማዋል ፈቃደኛ የሆነና ከዚህም ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ጢሞ 3:1-7፥ ቲቶ 1:6-9 የተገለጸውን ዝርዝር ሁኔታ የሚያሟላ መሆን አለበት።

8.6 በአንቀጽ 4.1 ዓላማ መሠረት ይህች ቤተክርስቲያን የቆመችለትን ዓላማ የተረዳና የሚያውቅ ለተግባራዊነትም የሚተጋ እንዲሁም ለምዕመናን መንፈሳዊ አንድነት የሚሠራ። ፊል 2:22-24፥ ቆላ 4:12-13

8.7 ጌታን ከተቀበለ ቢያንስ 5 አመት የሆነውና በየትም ሥፍራ በቤተክርስቲያን በሚሰጡት በተለያዩ አገልግሎቶች ቢያንስ ለሶስት ዓመት ሲያገለግል የቆየ ሊሆን ይገባዋል።

8.8 ቁጥር 8:7 እንደተጠበቀ ሆኖ ከሌላ ስፍራ የሚመጣ አገልጋይ የቤተክርስቲያኒቱ የሽማግሌነት እጩ ለመሆን በቤተክርስቲያኒቱ አንድ ዓመት ያህል የቆየና ከነበረበት ቤተክርስቲያን በታማኝነት ለረጅም ጊዜ በአገልግሎት ላይ የቆየ እንዲሁም መልካም ምስክርነት ያለው ሊሆን ይገባል። መሸኛም ከነበረበት ቤተክርስቲያን ያለው ሊሆን ይገባል።

8.9 አሥራቱን በታማኝነት የሚሰጥ፥

8.10 ጾታ አይለይም።

## አንቀጽ 9

## የሽማግሌ ምርጫ

9.1 የቤተክርስቲያኒቱ ሽማግለዎች ቁጥር ከሶስት አያንስም ከሰባት አይበልጥም።

9.2 የቤተክርስቲያኒቱን ሽማግለዎች ምርጫ በተመለከተ፦

የቤተክርስቲያኒቱ ሽማግለዎች ቦርድ አገልጋዮችና ምዕመናን ምርጫው እስከሚከናወንበት ጊዜ ድረስ ቤተክርስቲያን በምትሰጠው መመሪያ መሠረት በጾምና በጸሎት እንዲቆዩ ያደርጋል።

9.3 **ቦርዱ የሽማግሌዎች ጊዜያዊ አስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል።**

9.3.1 **አስመራጭ ኮሚቴ የሚያካትተው፥ ዋናውን የቤተክርስቲያን መጋቢ፥ ቦርዱ የሚወክላቸው ሁለት አባላትና ከምዕመናን መካከል በሽማግሌዎች ቦርድ የሚመረጡ እስከ አራት አባላት ይሆናሉ።**

9.3.2 **አስመራጭ ኮሚቴው ዕጩ ሽማግሌዎችን ከምዕመናንና ከአገልግሎት ቡድኖች መካከል ከተቀበለ በኋላ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የምርጫ ሂደቱን ያካሂዳል፥ የደረሰበትንም ውጤት ለቦርዱ ያቀርባል።**

9.4 **ቦርዱ አስመራጭ ኮሚቴው ያቀረባቸውን እጩዎች በጥሞና ከመረመረ በኋላ ያመነባቸውንና ያጸደቃቸውን እጩዎች ለምዕመናን ያቀርባል፥**

9.5 የተመረጡትን ሽማግሌዎች ለአባላቱ ያስታውቃል። አባላት በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ ካላቀረቡ ለአባላት በማስታወቅ ያስጸድቃል።

## አንቀጽ 10

## የአገልግሎት ዘመን

10.1 የሽማግሌዎች የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል።

10.2 የአንድ የሽማግሌ የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን ከነባር ሽማግሌዎች ሦስት ወይም አራት ወደሚቀጥለው የአገልግሎት ዘመን እንዲሻገሩ በማድረግ በአንቀጽ 9 መሠረት ሌሎች አዲስ ሽማግሌዎች እንዲሾሙ ይደረጋል። ሆኖም ግን ከቀሩት ነባር ሽማግሌዎች ለሥራው አስፈላጊ ቢሆኑም ለሁለት ዓመት ማረፍ አለባቸው።

## አንቀጽ 11

## የሽማግሌዎች ቦርድ የሥራ ኃላፊነትና ተግባር

11.1 **የሽማግሌ ቦርድ ማለት ሙሉ ድምጽ ያላቸው በአባላት የተመረጡ ሽማግሌዎችና የቤተክርስቲያኒቱ ዋና መጋቢ ይሆናል።**

11.2 የቤተክርስቲያኒቱ ሽማግለዎች ቦርድ የቤተክርስቲያኒቱ ህይወትና ጤና በእግዚአብሔር ቃል መሠረት እንዲጠበቅና እንዲመራ ያደርጋል። እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን የሰጠውንም ራዕይ በሥራ እንዲተረጎም ያደርጋል። የሐዋ ሥራ 15:22 ቲቶ 1:5። **በማንኛውም የመንግሥት አካል ሆነ በሌላ፥ ቤተክርስቲያንን በተመለከተ ለሚነሳው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ወይም የቤተክርስቲያንን ጉዳይ ለማስፈጸም ሀላፊነቱ የሽማግሌዎች ቦርድ ይሆናል።**

11.3 ቦርዱ የቤተክርስቲያኒቱን መንፈሳዊ ፕሮግራሞች ዝርዝር አሰራርና እንቅስቃሶዎች በተመለከተ ለእረኛው አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፥ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል። እንዲሁም የአስተዳደር ሥራዎችን በሙሉ ኃላፊነት ይሠራል።

11.4 ቦርዱ የቤተክርስቲያኒቱን የሂሣብ አያያዝ መመሪያ (Financial Manual) ያዘጋጃል።

11.5 ቦርዱ የቤተክርስቲያኒቱን እቅድ፥ በጀት፥ ሂሳብና ንብረት በማዘጋጀት በመቆጣጠር በሥራ ላይ ያውላል። ማንኛውም ወጪና ገቢ በሚወጣው (Financial Manual) መሠረት መንቅሳቀሱን ይቆጣጠራል።

11.6 ቦርዱ የቤተክርስቲያኒቱን የእለት እለት ሥራውን የሚያከናውነው በእረኛው አማካይነት ነው። እረኛውም ለከንውኖቹ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል።

11.7 የቤተክርስቲያኒቱ ሽማግለዎች እረኛው ምዕመናንን በወንጌል ትምህርት ለማሳደግ በሚያደርገው ጥረት ይተባበራሉ። እንደተሰጣቸውም ጸጋ በተለያዩ አገልግሎቶች ይሰማራሉ። 1ኛ ጴጥ 5:2፥ ያዕ 5:14-15፥ 1ኛ ጢሞ 5:17

11.8 የቤተክርስቲያኒቱ ሽማግለዎች ቦርድ በአንቀጽ 4 የተጠቀሱትን የቤተክርስቲያኒቱን ዓላማ በሥራ እንዲተረጎም ይተጋሉ። 1ኛ ጴጥ 5:2-5

11.9 ቦርዱ የቤተክርስቲያኒቱን ዓመታዊ የሥራ እቅድና በጀት በማዘጋጀት ለምዕመናን በማቅረብ ያጸድቃል።

11.10 የቤተክርስቲያኒቱን ሒሳብ የሚመረምር የውስጥ ሒሳብ መርማሪ (ኦዲተር) ይመድባል። የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችንም ለማግኘት እንዲቻል በመንግሥትም ዘንድ ተጠያቂነት እንዳይኖር በCPA የቤተክርስቲያኒቱ ሂሳብ በየዓመቱ እንዲመረመር ተገቢውን ክትትል ያደርጋል።

11.11 ለቤተክርስቲያኒቱ የሚያስፈልገውን እረኛ ያስመርጣል። በምዕመኑም ፊት አቅርቦ ያፀድቃል።

11.12 ለቤተክርስቲያኒቱ አስፈላጊ የሆኑትን ዲያቆናት ይመርጣል። የሐዋ ሥራ 6:1-6፥ ፊል 1:1፥ 1ኛ ጢሞ 3:9-13

11.13 በዓመት ሁለት ጊዜ በሚደረጉት የአባላት ስብሰባ ላይ የቤተክርስቲያኒቱን የሥራና የሒሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት ያቀርባል።

11.14 የእረኛውንና የሌሎች ሠራተኞችን ደመዎዝና አስፈላጊውን ጥቅማ ጥቅሞችን ይወስናል፡ የአገልግሎት ብቃትን በመገምገም እንደ ቤተክርስቲያኒቱ አቅም የደመውዝ ጭማሪ ያደርጋል።

11.15 የሽማግሌዎች ቦርድ እንዳስፈላጊነቱ የአገልግሎት ክፍሎችን ያቋቁማል፥ የአገልግሎት ቡድን መሪ ወይም ተጠሪዎችን ይሰይማል።

11.16 የሽማግለዎች ቦርድ የቤተክርስቲያኒቱን ሠራተኞች የደሞዝ እርከን (Scale) ያወጣል።

11.17 ቦርዱ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የትርጉም ጥያቄ ቢነሣ ለጥያቄው ተገቢውን መልስ ይሰጣል።

11.18 ቦርዱ የአጭር የመሀከለኛና የረዥም ጊዜ የሥራ ዝርዝር ዕቅድ ያዘጋጃል።

11.19 ቤተክርስቲያኒቱ ከአቅም በላይ የሆነ የውስጥ ችግር ቢያጋጥማትና ቦርዱ መፍትሔ መስጠት ቢያቅተው -

ሀ) ከምዕመኑ መካከል እንደሁኔታው በመሪነት ያገለገሉትን አባላትን ከ5-7 ሰዎች መርጦ ኮሚቴውን ያቋቁማል። **ከዚያም ኮሚቴው የደረሰበትን ውሳኔ ለጉባኤው ያቀርባል።**
ለ) ከባፕቲስት ኮንቬንሽን እርዳታ በመጠየቅ፥
ሐ) ከላይ በተጠቀሱት አሠራር ሁኔታው የማይፈታ ከሆነ ቦርዱ ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም መፍትሔ ይፈልጋል።

11.20 የቤተክርስቲያኒቱን ሥነስርዓት የማስከበር ሥልጣን የሽማገለዎች ቦርድ **ይሆናል**። የሚወሰዱትም ሥነስርዓታዊ እርምጃዎች አላማቸው ምዕመኑን ለመገንባትና ለማነጽ ይሆናል።

11.21 ሥነስርዓታዊ እርምጃው ጾታ ወይም እድሜ ሳይወስነው ከላይ እስከታች በተዋረድ ያለ አድልዎ በእኩልነት በአንቀጽ 4.1.2.11 መሠረት ይፈጸማል። 1ኛ ጢሞ 5:21፥ ገላ 2:4-6፥ የሐዋ ሥራ 10:34-35፥ ሮሜ 2:11፤ 11.21

11.22 በአንቀጽ 11.19 እና 11.20 መሠረት ሥነ ስርዓታዊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

## አንቀጽ 12

## የሽማግሌዎች ቦርድ ስብሰባ

12.1 የሽማግሌዎች ቦርድ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ የሚያካሂድ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱም በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

12.2 የሽማግሌዎች ቦርድ አባላት 2/3 ኛው እጅ በተገኙበት ጊዜ ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል።

12.3 የቤተክርስቲያኒቱ የሽማግሌዎች ቦርድ ውሳኔ የሚጸድቀው በድምጽ ብልጫ ይሆናል። ቦርዱ ውሳኔ ለማድረግ እኩል ሆኖ በሚከፈልበት ጊዜ የሰብሳቢው ድምጽ የመጨረሻ ይሆናል።

## አንቀጽ 13

## የሽማግሌ መገለል ወይም ስንብት

13.1 ማንኛውም የሽማግሌዎች ቦርድ አባል በራሱ ፍላጎት አገልግሎቱን መልቀቅ ቢፈልግ ይህንኑ በጹህፍ ከሰላሳ ቀናት በፊት ለሽማግሌዎች ቦርድ ሲያቀርብ ጉዳዩ ታይቶ ተገቢው ይፈጸማል የተወሰደው እርምጃ ለቤተክርስቲያን ምዕመናን ይገለጻል።

13.2 ማንኛውም የሽማግሌዎች ቦርድ አባል ያለ በቂ ምክንያት የቦርዱ ስብሰባ ላይ በተከታታይ ለሦስት ጊዜ ቢቀር በቅድሚያ ችግሩን በመጥየቅ፥ በመምከር፥ በመገሰጽና በማስጠንቀቅ ምክንያቱን አጢኖ ውጤቱ ካልተሻሻለ በመጨረሻ በሽማግሌዎች ቦርድ ከተጠና በኋላ ከአገልግሎቱ ይገለላል። የተወሰደውም እርምጃ ለቤተክርስቲያን ምዕመናን ይገለጻል። ኤር 48:10

13.3 የሽማግሌዎች ቦርድ አባል የቤተክርስቲያኒቱን ሕግ ሲተላለፍ እንዲሁም የሞራል ውድቀት፥ የእምነት፥ ግድፈት የቤተክርስቲያኒቱን ምስጢር የማባከን፥ የቤተክርስቲያኒቱን አንድነት የሚያናጋና ሕብረቱን የሚጻረር ተግባር በቃልና በሥራ ሲፈጽም ቢገኝ ጉዳዩ እስኪጣራ ላልተወሰነ ጊዜ ከሽማግሌዎች ቦርድ ይገለላል።የሽማግሌዎች ቦርድ ጉዳዩን አጥንቶ ካረጋገጠ በኋላ ከቦርዱ አባልነት ይገለላል። የተወሰደውም እርምጃ ለቤተክርስቲያኒቱ ምዕመናን ይገለጻል። 2ኛ ጴጥ 2:2-3፥ 1ኛ ጢሞ 1:20፥ የሐዋ ሥራ 20:29-30

## አንቀጽ 14

## የሽማግሌውች ቦርድ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ የሥራ ኃላፊነትና ተግባር

14.1 የሽማግሌውች ቦርድ ሰብሳቢ ዋናው መጋቢ ይሆናል።

14.2 የቦርዱን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል።

14.3 የቤተክርስቲያኒቱን ጠቅላላ ጉባኤ ከምክትል ሰብሳቢው ጋር ስብሰባ ይመራል። የቤተክርስቲያኒቱን ዘገባ ያቀርባል፤ ያወያያል አስተያየቶችን ይቀበላል።

14.4 የቤተክርስቲያኒቱን ውሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል።

14.5 ምክትል ሰብሳቢው ከሽማግሌዎች መካከል በድምጽ ብልጫ ይመረጣል።

14.6 ዋናው ሰብሳቢ በሌለበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው ከላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች ተክቶ ይሰራል።

## አንቀጽ 15

## የሽማግሌዎች ቦርድ ጸሐፊ

15.1 የሽማግሌዎች ቦርድ ጸሐፊ ከሽማግሌዎች መካከል በድምጽ ብልጫ ይመረጣል።

15.2 በሚሰጠው ውስጣዊ መመሪያ መሠረት የውይይት አጀንዳዎችን አጠናቅሮ በሽማግሌዎች ቦርድ ስብሰባ ላይ ያቀርባል።

15.3 የሽማግሌዎች ቦርድና የአባላት ምልዓተ ጉባኤ ስብሰባዎች በሚደረጉበት ጊዜ ቃለ ጉባኤዎችን፥ ውሳኔዎችን፥ ትእዛዞችንና ኃሳቦችን በጽሁፍ አስፍሮ በመመዝገብ ይይዛል። ቃለ ጉባኤውንም አዘጋጅቶ የቦርድ አባላትን ያስፈርማል።

15.4 ክትትል የሚያስፈልጋቸውን ውሳኔዎች በተግባር ላይ መዋልና አለመዋላቸውን በቦርዱ ስብሰባ ላይ ያሳስባል።

15.5 ዋና ጸሃፊው የቤተ ክርስቲያኒቷን ሂሳብ ከምክትል ሰብሳቢውና ከሂሳብ ሹሙ ጋር በመሆን ያንቀሳቅሳል።

## አንቀጽ 16

## የዲያቆናት ብቃት

16.1 እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት 1ኛ ጢሞ 3:8-13 የተጠቀሱትን ዝርዝር ሁኔታዎች የሚያሟሉ መሆን አለባቸው።

16.2 እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት በመልካም የተመሠከረላቸው መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላባቸው እንዲሆኑ ይገባል። የሐዋ ሥራ 6:3

16.3 የዲያቆናት ባህርይ፡-

ሀ) ጭምት፥ ቅን፥ ትሁት፥ ለመምከር የሚበቃ

ለ) በንግግር አንጻር በሁለት ቃል የማይናገሩ የማያወላውሉ፥ አስበው የሚወስኑና በወሰኑት የሚጸኑ (ሆኖም ግትር

ያልሆኑ)

ሐ) በሞራል አንጻር የማይሰክሩ (አልኮል የማይጠጡ) ስስታም ያልሆኑ በክፋትና በማታለል ያልተሰማሩ።

መ) በቁም ነገረኝነት አንጻር ሚስጥርን የሚጠብቁ፥ የሚያውቁትን ለማይመለከተው የማይናገሩ (ለትዳር ጓደኛም ቢሆን)

ሠ) በትዳር አንጻር እያንዳንዳቸው የአንዲት ሴት ባሎች የሆኑ (1ኛ. ሴት አትሆንም ማለት አይደለም፥ 2ኛ. ሌሎች ምዕመናን ብዙ ሚስት ይኑራቸው ማለት አይደለም፥ 3ኛ. ሚስት የሌለው አይበቃም ማለት አይደለም)

ረ) የተፈተኑ የሚለው ከላይ በተገለጡት ነገሮች በዓመታት ውስጥ ተፈትነው የታዩ ማለት ነው። የሐዋ ሥራ 6:3

## አንቀጽ 17

## የዲያቆናት ምርጫ እና የአገልግሎት ዘመን

17.1 የሽማግሌዎች ቦርድ የዲያቆናት እጩዎችን ይመርጣል።

17.2 የሽማግሌዎች ቦርድ የቀረቡትን የእጩዎች ስም ዝርዝር ተመልክተው ካጤኑትና ከጸለዩበት በኋላ በእያናዳንዱ ተመራጭ ላይ ኃሳብ ያቀርባሉ።

17.3 የሽማግሌዎች ቦርድ የተስማሙባቸውን እጩዎች በቤተክርስቲያኒቱ አባሎች ፊት በማቅረብና በማስጸደቅ ይሾማል።

17.4 የሽማግሌውች ቦርድ የቤተክርስቲያኒቱን ዲያቆናት ቁጥር ይወስናል። ቁጥራቸውም እስከ ሰባት ይሆናል።

17.5 የዲያቆናትን ጉባኤ ሰብሳቢና ጸሐፊ ቦርዱ ከዲያቆናት መካከል ይመርጣል።

17.6 የዲያቆናት ጉባኤ ስለአገልግሎታቸው በወር አንድ ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

17.7 የዲያቆናት የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል።

17.8 የአንድ ዲያቆን የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ቢሆንም በአገልግሎት ዘመን መጨረሻ እንደገና ለሁለት ዓመት ሊመረጥ ይችላል። ሆኖም ለሁለት ዘመን ምንም እንኳን ለሥራው አስፈላጊ ቢሆንም አንድ የአገልግሎት ዘመን ማረፍ አለበት። ሆኖም የአገልግሎት ልምዳቸውን ለማካፈል ከሶስት የማያንሱት ለሌላ ሁለተኛ የአገልግሎት ዘመን ሊመረጡ ይችላል።

## አንቀጽ 18

## የዲያቆናት የሥራ ኃላፊነትና ተግባር

18.1 ማንኛውንም የቤተክርስቲያኒቱን የምዕመናን ጉባኤ ስብሰባዎችን በሥርዓት ያስተናግዳሉ።

18.2 እንደ እግዚአብሔር ቃል መሰረት (የሐዋ ሥራ 6:2-6) በቤተክርስቲያኒቱ የአንድነት ጊዜና በመሳሰሉት ዝግጅቶች ላይ ያገለግላሉ።

18.3 ጉብኝት የሚያሻቸውን ወገኖች እየተዘዋወሩ ይጎበኛሉ፥ በእግዚአብሔር ቃል ያጽናናሉ፥ ይከታተላሉ ልዩ ልዩ ጉዳይችን እንደ አስፈላጊነታቸው ለሽማግሌዎች ቦርድ ያቀርባሉ። የሐዋ ሥራ 6:8-10

18.4 በቤተክርስቲያን የሚሰበሰበውን መባ፥ አሥራትና ስጦታ ቆጥረው በማስረጃ በዕለቱ ለገንዘብ ያዥው ያስረክባሉ።

18.5 የቤተክርስቲያኒቱ ንብረት በመዝገብ ተመዝግቦ መያዙንና መጠበቁን ያረጋግጣሉ።

18.6 ችግረኞችን እንደ አስፈላጊነቱና አቅም እንደፈቀደ ከሽማግሌዎች ቦርድ ጋር በመመካከር ይረዳሉ። የሐዋ ሥራ 6:3-5 በመዋቅሩ መሠረት የሚያግዟቸውን ኮሚቴዎች ያቋቁምል።

18.7 የቤተክርስቲያኒቱ የሽማግሌዎች ቦርድ በሚሰጣቸው መመሪያ መሰረት አስፈላጊውን የሥራ ኃላፊነት በታማኝነት ያከናውናሉ።

18.8 በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚፈጸሙትን የጌታ እራትና የውኃ ጥምቀት የመሳሰሉ ሥርዓቶችን ለማስፈጸም አስፈላጊውን ዝግጅት ያደርጋሉ።

18.9 የዲያቆናት ጉባኤ ተጠሪነቱ ለሽማግሌዎች ቦርድ ይሆናል።

## አንቀጽ 19

## የዲያቆናት መገለል ወይም ስንብት

19.1 ማናቸውም የዲያቆናት ጉባኤ አባል በፈቃደኝነት አገልግሎቱን ለመልቀቅ ሲወስን ጉዳዩን በጽሑፍ ለሽማግሌውች ቦርድ ሲያቀርብ ሁኔታው ከተጠናቀቀ በኋላ እንዳስፈላጊነቱ ውሳኔ ይሰጣል።

19.2 ዲያቆኑ ያለ በቂ ምክንያት ከአገልግሎቱ ላይ ከሦስት ወይም ከአራት ጊዜያት በላይ በተከታታይ ቢቀር ጉዳይ በዲያቆናት ጉባኤ በኩል ለሽማግሌዎች ቦርድ ሲቀርብ በቅድሚያ ችግሩን በመጠየቅ በመምከር በመገሰጽና በማስጠንቀቅ ምክንያቱን አጢኖ ውጤቱ ካልተሻሻለ በመጨረሻ ከአገልግሎቱ ይወገዳል። ኤር 48:10

19.3 ዲያቆኑ የቤተክርስቲያን ሕግ ሲተላለፍ እንዲሁም የሞራል ውድቀት፥ የእምነት ግድፈት፥ የቤተክርስቲያኒቱን ሚስጢር የሚያባክን፥ የቤተክርስቲያኒቱን አንድነት የሚያናጋና ሕብረቱን የሚጻረር ተግባር በቃልና በሥራ ሲፈጽም ቢገኝ ጉዳዩ እስኪጣራ ላልተወሰነ ጊዜ ከዲቁናነቱ ያርፋል። የሽማግሌውች ቦርድ ጉዳዩን አጥንቶ ካረጋገጠ በኋላ ከዲያቆንነት ይገለላል። 2ኛ ጴጥ 2:2-3፥ የሐዋ ሥራ 20:29-30፥ 1ኛ ጢሞ 1:20

19.4 የሽማግሌዎች ቦርድ እንደ አስፈላጊነቱ በመገለል ላይ ያለውን ዲያቆን በሕይወቱ ተሐድሶ እንዲያገኝ የሚቻለውን ጥረት ያደርጋሉ።

## አንቀጽ 20

## የእረኛ ብቃትና ችሎታ

20.1 በመንፈስ ቅዱስ የተቀባና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማገልገል መለኮታዊ ጥሪ ያለው፥ ኤፌ 4:11፥ የሐዋ ሥራ 20:28፥ የሐዋ ሥራ 13:1-2 1ኛ፥ 1ኛ ቆሮ 12:28 ዮሐ 21:15-17

20.2 እንደ እግዚአብሔር ቃል የእረኝነት መስፈርትን የሚያሟላ፥ 1ኛ ጢሞ 3:1-7፥ ቲቶ 1:6-9፥ 1ኛ ጴጥ 5:1-4፥ 1ኛ ጢሞ 1:1-7

20.3 ራሱን ለአገልግሎት አሳልፎ የሰጠ፥ ፊል 2:22-24

20.4 ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ላላወቁና ላልሰሙ ወንጌልን ለማሰራጨት ሸክም ያለው፥ ማቴ 18:12-14

20.5 ጤናማ ትምህርት በመስጠት ምዕመናንን የሚንከባከብና የሚያሳድግ፥ 1ኛ ጢሞ 5:17፥ 4:16፥ 6:9-12፥ ቲቶ 1:9፥ 2:7-8፥ 1ኛ ጴጥ 5:17፥ 1ኛ ጢሞ 5:1-4፥ ዮሐ 21:15-17

20.6 በቤተክርስቲያኒቱ መሠረተ እምነት በሙሉ የሚያምንና የመተዳደሪያ ደንቡንም የሚያከብር፥

20.7 በየትኛውም የአገልግሎትር ዘርፍ ተሰጥዖና ዝንባሌ ያላቸውን አገልጋዮች ተተኪ መሪዎች እንዲሆኑ ለማብቃት ራዕይ ያለውና አስፈላጊውንም እገዛ የሚያደርግ፥

20.8 መለኮታዊ ጥሪው እንደተጠበቀ ሆኖ በትምህርተ መለኮት ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለውና እንዲሁም በእንጊሊዝና ቋንቋ በቂ ችሎታ ያለው ሊሆን ይገባል።

20.8.1 ቢያንስ በመጋቢነት አምስት ዓመት ያገልግሎት ልምድ ያለው ሊሆን ይገባል።

20.9 መልካም የአገልግሎት፥ የህይወትና የቤተስብ ምሥክርነት ያለውና ማስረጃም ማቅረብ የሚችል፥

20.10 የቤተክርስቲያኒቱን መተዳደሪያ ደንብ የሚቀበልና ለተግባራዊነቱም የሚተጋ፥

20.10.1 ቢያንስ ለዓምስት ዓመታት ለማገልገል ፈቃደኛና ራሱን የሠጠ ሊሆን ይገባል።

## አንቀጽ 21

## የዋና እረኛው (Senior Pastor) የሥራ ኃላፊነትና ተግባር

21.1 ዋናው እረኛ ተጠሪነቱ ለቤተክርስቲያኒቱ የሽማግሌዎች ቦርድ ይሆንና የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

21.1.1 ቤተክርስቲያኒቱን በተመለከተ ማንኛውም ጥያቄ ቢነሳ ከቦርዱ ጋር በመመካከር ተገቢውን ይፈጽማል፥

21.1.2 ለቤተክርስቲያኒቱ የሚያስፈልጉትን የልዩ ልዩ የአገልግሎት ኮሚቴ አገልጋዮች ከሽማግሌዎች ጋራ በማጣራትና በመመካከር ይመርጣል ያስመርጣል።

21.1.3 እረኛው ምዕመኑን ለመጠበቅ፥ ለማጽናናት፥ ለማስተማር፥ ለመምከር፥ ለመገሰጽ የጠፋውን ለመፈለግና ምሳሌ ለመሆን ይተጋል። ኤር 3:15፥ ዮሐ 21:15-17፥ የሐዋ ሥራ 20:28፥ 1ኛ ጢሞ 4:11-13

21.1.4 ለቤተክርስቲያኒቱ ጠቃሚ የሆኑ ተግባሮችን እንዲሁም በሽማግሌዎች ቦርድ አማካይነት የሚተላለፍ ሥራዎችን በእርሱ በኩል መፈጸም ያለበትን ይፈጽማል፥ በሌሎች በኩል መፈጸም ያለበትን ያስፈጽማል።

21.1.5 እረኛው የቤተክርስቲያኒቱ አገልጋዮች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በእግዚአብሔርና በሕዝብ ፊት መፈጸም እንዲችሉ ያበረታታል።

21.1.6 በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ መከናወን ያለባቸውን መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች በሙሉ ይመራል፥

ያስተባብራል።

21.1.7 የቤተክርስቲያኒቱን ምዕመናን ጤናማ ሕይወት ለመጠበቅ ሲባል ምዕመናን የቤተክርስቲያንን የመንፈስ አንድነት ከሚያናጋና የስህተት ትምህርትን ለማስተላለፍ ከሚደረጉ መንፈሳዊ ስብሰባዎችና እንዲሁም ከሚያስፈጽሙ አገልጋዮች መታቀባቸውን ከሽማግሌዎች ጋር በመሆን ይቆጣጠራል።

21.1.8 የቤተክርስቲያኒቱ የአገልግሎት ክፍሎች የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ በሽማግሌዎች ቦርድ ከጸደቀ በኋላ እረኛው በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል።

21.1.9 ቤተክርስቲያኒቱ ከቴክሳስ ባፕቲስት ኮንቬንሽን ጋር ባላት ግንኙነት መሠረት በየዓመቱ በሚደረገው የጋራ ስብሰባ ላይ እንዳስፈላጊነቱ ከቦርዱ አባላት ጋር በመመካከር መገኘት።

21.1.10 ጠቃሚ ትምህርቶች ይገኙበታል ተብለው በሚታመኑባቸው የተለያዩ መሰል አብያተ ክርስቲያናት ስብሰባ ላይ መገኘት።

21.1.11 የአጥቢያይቱን አገልግሎት በማይጎዳ መልኩ የቤተክርስቲያንን አድማስ ለማስፋት እንዲቻል ከማንኛውም መሰል ቤተክርስቲያን ጋር ግንኙነት ማድረግ።

21.1.12 መንፈሳዊ ትምህርትና ሥልጠና ለሚፈልጉ የቤተክርስቲያኒቱ አገልጋዮችና አባላት አስፈላጊውን ጥናት በማድረግ ለሽማገሌዎች ቦርድ እያቀረበ ያስፈጽማል።

21.1.13 ዓመታዊ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለሽማግሌ ቦርድ ማቅረብ። በእቅዱም ውስጥ በቤት ክርስቲያን የሚሰጠውን ትምህርት (Curriculum) ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች (Events) ሪትሪትና የወንጌል ሥርጭት የመሳሰሉትን ማካተት።

21.1.14 የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በተመለከተ በዕቅዱ መሠረት የተከናወኑትንና ያልተከናወኑትን የሥራ አፈጻጸም በዓመት ሁለት ጊዜ ሪፖርት ለሽማግሌዎች ቦርድ ያቀርባል።

## አንቀጽ 22

## ሹመት

22.1 አንድ አገልጋይ የእረኝነቱን ሹመት ከመቀበሉ በፊት በአንቀጽ 20 የተዘረዘሩትን ሲያሟላ የጥሪው እውነተኝነት፥ ስጦታውና ችሎታው በቤተክርስቲያኒቱ የሽማገሌዎች ቦርድ ሊታመንበት ይገባል።

22.2 **የሽማግሌዎች ቦርድ ዋናውን መጋቢ ለመምረጥ የሶስት ሳምንት ጊዜ ይሰጣል፥ በዚህ ጊዜ ውስጥ ምርጫውን በተመለከተ ተገቢ ትምህርት ይሰጣል።** የሽማግሌዎች ቦርድ የአባሎች ስብሰባ በመጥራት ለምዕመናን ስለ አገልጋዩ ጥሪ እውነተኛነትና ስጦታ የሚያውቁትንና በመንፈስ የተረዱትን በመግለጽ አባላቱ ስለአገልጋዩ ድምጽ እንዲሰጡ ያደርጋል።

22.3 አገልጋዩ ሹመት ለመቀበል ይገባዋል ወይም አይገባውም በማለት ድምጽ ለመስጠት ቢያንስ ከአባሎች ¾ ኛው እጅ መገኘት ይገባዋል። የማይገኙ ከሆነ የሽማግሌዎች ጉባኤ ለሁለተኛ ጊዜ ስብሰባ ይጠራል። በተገኙትም አባላት 2/3 ከመረጠው ያገልጋዩ ሹመት ይጸድቃል።

## አንቀጽ 23

## የእረኛው መብት

23.1 እረኛው ደመወዙን ከቤተክርስቲያን ይቀበላል።

23.2 እረኛው ከሽማገሌዎች ጋር በመመካከር ውስጠ ደንብ በሚያዘው መሰረት እረፍት ይወስዳል።

## አንቀጽ 24

## የአገልግሎት ዘመን

24.1 እረኛው የማስተዋል ችሎታው ጠንካራ ሆኖ የዝንጉነት አዝማሚያ ካልታየበት በስተቀር እድሜው 67 ዓመት እስኪሆን ሊያገለግል ይችላል።

24.2 እረኛው ከአገልግሎት ለማረፍ ከ2-3 ዓመት ሲቀረው ለሽማግሌዎች ቦርድ ለእረኝነት ብቁ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ዕጩዎች ያቀርባል።

## አንቀጽ 25

## ከሥራ የመገለል ሁኔታዎች (ምክንያቶች)

25.1 እረኛው በፈቃዱ ኃላፊነቱን ለመልቀቅ ቢፈልግ ጉዳዩን ለሽማግሌዎች ቦርድ ከ90 ቀኖች በፊት በማቅረብ ይኸው ሁኒታ በሽማግሌዎች ቦርድ ከተጠና በኋላ ከሃላፊነቱ መሰናበት ይችላል።

25.2 እረኛው ያለ በቂ ምክንያት በመደጋገም ከሥራ ገበታው ላይ ሳይገኝ ቢቀር የሽማግሌዎች ቦርድ በቅድሚያ ችግሩን በመጠየቅ በመምከር በመገሰጽና በማስጠንቀቅ ምክንያቱን አጢኖ ውጤቱ ካልተሻሻለ በመጨረሻ የደረሰበትን ውሳኔ 2/3ኛው እጅ ከደገፈ ከእረኝነት ሥራው ይሰናበታል፥ ሁኔታውም ለምዕመን ይገለጻል። ኤር 48:10፥ 23:2፥ 1ኛ ሳሙ 16:1፥ ነህ 13:7-9

25.3 እረኛው የቤተክርስቲያኒቱን ሕግ ሲተላለፍ የሞራል ውድቀት ወይም የእምነት ግድፈት ሲገኝበትና ይህም ቢያንስ በሁለት ወይም በሶስት ምስክር ሲረጋገጥና የቤተ ክርስትያኒቱ መሪዎች ሲያምኑበት ወዲያው ከእረኝነት ሥራው ይገለላል ይህም ውሳኔ ለምዕመኑ ይገለጻል።

25.4 እረኛው በተሰጠው ውሳኔ ባይስማማ **የቤተክርስቲያን የሽማግሌዎች ቦርድ** ከቤተክርስቲያኒቱ ምዕመን የተውጣጡ ልዩ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሁኔታውን እንዲያዩ ይደረጋል።

25.5 የሽማግሌዎች ቦርድ እንደ አስፈላጊነቱ የተሰናበተውን እረኛ በሕይወቱ ተሐድሶ እንዲያገኝ የሚችለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል።

25.6 እረኛው አገልግሎቱንና የስራ ሃላፊነቱን በሚገባ አለመወጣቱ ሲታወቅ ከተደጋጋሚ የቃልና የጽሁፍ ምክሮች ማስጠንቀቂያ በኋላ ባይሻሻል በሚወጣው ዝርዝር የሥራ መመሪያ መሠረት ይሰናበታል።

## አንቀጽ 26

## ተባባሪ እረኛ (Associate Pastor)

26.1 የተባባሪ እረኛው ብቃትና ችሎታ:-

26.1.1 የተባባሪ እረኛው ብቃትና ችሎታ በአንቀጽ 20 ላይ እንደተጠቀሰው ሲሆን ሹመቱም የሚጸናው በሽማግሌዎች ቦርድ ከታመነበት በኋላ ነው። ቢያንስ በሥነመለኮት የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው፥

26.1.2 የተባባሪ እረኛው ሹመት ሙብት፥ የአገልግሎት ዘመንና ከሥራ መገለል ከአንቀጽ 22 እስከ 25 እንደተጠቀሰው ይሆናል። (ሆኖም አንቀጽ 24.2 አይመለከተውም)

26.2 የተባባሪ እረኛው ኃላፊነትና ተግባር:-

26.2.1 ዋናው እረኛ በማይኖርበት ጊዜ የሽማግሌዎች ቦርድ ኃላፊነቱን በመውሰድ በአንቀጽ 21 ላይ የተዘረዘረውን ሥራ እንዲቀጥል ያደርጋል። እንዳስፈላጊነቱም የሽማግሌዎች ቦርድ ለተባባሪ እረኛው የሥራ ዝርዝር በመሥጠት አገልግሎቱ እንዲቀጥል ያደርጋል።

26.2.2 ተጨማሪ ሥራዎችን በዋናው መጋቢ በሚሰጠው መመሪያና የሥራ ዝርዝር መሠረት ይፈጽማል።

## አንቀጽ 27

## ቤተክርስቲያኒቱ ያለዋና (senior) እረኛ በምትሆንበት ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃዎች

27.1 ቤተክርስቲያኒቱ ዋና እረኛ (Sinior Pastor) ከሌላት ለቤተክርስቲያኒቱ መሪና ተጠያቂ በመሆን የቤተክርስቲያኒቱ የሽማግሌዎች ቦርድ ምክትል ሰብሳቢ ይመራል። ይህም ቤተክርስቲያኒቱ እረኛ እስክትሾም ድረስ ይሆናል፣ ለቤተክርስቲያኒቱ አባላትም ጉዳይ ይገለጻል።

27.2 የተፈለገው እረኛ ካልተገኘ የሽማግሌዎች ቦርድ በቤተክርስቲያኒቱ እንዲጸለይበት ካደረገ በኋላ መለኮታዊ ጥሪ ያለውን እጩ እረኛ በጥንቃቄ በመለየት ፍሊጋው እንዲቀጥል ይደረጋል።

27.3 የሽማግሌዎች ቦርድ ለቤተክርስቲያኒቱ አባላት የሚያቀርበው እጩ በቁጥር ከአንድ መብለጥ የለበትም። ይህም እጩ ግለሰብ ለአባላቱ የሚቀርበው በሽማግሌዎች ቦርድ በድምጽ ብልጫ ሲመረጥ ብቻ ነው።

27.4 የሽማግሌዎች ቦርድ አባላቱን በዚህ ጉዳይ ላይ ለማወያየት ከሁለት ሳምንት በፊት ጥሪ ያደርጋል።

27.5 የእረኛው ሹመት የሚጸድቀው በአንቀጽ 22.3 እንደተጠቀሰው ይሆናል።

## አንቀጽ 28

## የወጣት አገልግሎት (Youth Ministry)

የወጣት አገልግሎት ከሁለተኛ ደረጃ እስከ ኮሌጅ ያሉትንና ጎልማሳ ወጣቶችን ያጠቃልላ።

28.1 የወጣት አገልግሎት (Youthe Ministry) ዓላማ

28.1.1 የወጣቶች መጋቢ ከወላጆች፥ ከመምህራንና ከቤተክርስቲያኒቱ ዋና መጋቢ የአገልግሎት ክፍሎች ጋር ግንኙነት በማድረግ የሚያገለግላቸው ወጣቶች በእምነታቸው ሥር በመስደድ፡-

28.1.1.1 ከእምነታቸውና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከመውደድ ፈቀቅ እንዳይሉ ወይም እንዳይርቁ ማድረግ፤ ምሳ 22:6

28.1.1.2 የወደፊት የቤተክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች እንዲሆኑ በእግዚአብሔር ቃል እንዲያድጉ በቅርብ ሆኖ መከታተልና መምራት፣

28.1.1.3 ከዋናው መጋቢና ከመንፈሳዊ ትምህርት ዘርፍ ጋር በመመካከር የወጣቶችን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ያደራጃል፥ ሂደቱንም ይቆጣጠራል።

28.1.2 ወጣቶችን በመውደድ፥ በማክበር፥ ያለአድልዎ በችግራቸው እየገባ በማስተማር በመምከር፥ የጠፉትን ወይም ከቤተክርስቲያን የራቁትን ፈልጎ በማምጣት የወንጌል ጉዞን እንዲጓዝ መርዳት።

28.1.3 ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎቻቸውን እንዲሁም ወጣቶችን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መድረስ።

28.1.4 የቤተክርስቲያኒቱን ዋና መጋቢ በማማከር ወጣቶቹ በቅድስናና በጽድቅ በመኖር መልካም ቤተሰብ እንዲመሠርቱ ስለጋብቻ ማስተማርና፥ ማሰልጠንና ማዘጋጀት።

28.2 የወጣት መጋቢው (Youth Pastor) ኃላፊነትና ችሎታ፡-

28.2.1 የእግዚአብሔርና የቃሉ ፍቅር የበዛለት፥ ለወጣቶች ልዩ ፍቅር ያለው፥ መልካም የእረኝነት ልብ ያለው፣ ከዚህም የተነሳ የሚያገለግላቸው ወጣቶች ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያላቸው ግንኙነት እያደገ የሚሄድ መሆኑን በቅርብ ሆኖ የሚያይና የሚገነዘብ፥

28.2.2 ከቤተክርስቲያን መሪዎች፥ ወላጆች፥ መምህራንና ከራስቸው ከወጣቶች ጋር ጥሩ ግንኙነት ማድረግ መቻል።

28.2.3 ከማንኛውም የቤተክርስቲያኒቱ የአገልግሎት ክፍል ጋር (መጋቢዎች፣ ሽማግሌዎች፥ ዲያቆናት የመሳሰሉት) በፍቅር አብሮ መሥራት መቻል።

28.2.4 የሚያገለግላቸውን ወጣቶች ለጉብኝት ትኩረት በመስጠት በተናጠል (one to one) ወይም በትናንሽ ህብረት በመሆን እቅድ በማውጣት መንብኘት ያለባቸውን ችግሮች ተረድቶ በጸሎት፥ በምክርና በትህርት መርዳት መቻል።

28.2.5 ልዩ ልዩ በዓላትን ወይም ሁኔታዎችን በመጠቀም (ገና፥ ስቅለት፥ ሪትሪት ሌሎችም በዚህ ያልተጠቀሱ) ወጣቶችን በማደራጀትና በማስተተባበር ወጣቶችን ለመድረስ በወንጌል ስርጭት እንዲሳተፉና እንዲያከናውኑ ለመርዳት መቻል።

28.2.6 በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ከሚመለከታቸው ልዩ ልዩ አገልግሎት ዘርፍ ጋር በመሆን ለወጣቱ ካሪኩለም መንደፍ፥ ማሻሻልና ለተግባራዊነቱም በመትጋት የበላይ ሆኖ በመቆጣጠር ውይይት ማካሄድ። አስፈላጊም ከሆን ከሊሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ግንኙነት በማድረግ ልምድ ለማግኘት መሞከር።

28.2.7 ከመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ በክርስትና ትምህርት (Christian Education) ወይንም ከወጣቶች አገልግሎት (Youth Ministry) ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው።

28.2.8 የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታው ያላቀ ሆኖ በፍሰት መናገር፥ መስበክ፥ መጻፍ የሚችል፣ ቢቻል የአማርኛ ቋንቋ እውቀት ያለው።

28.2.9 ለወጣቱ አገልግሎት ላይ ትኩረት በመስጠት እየተጠናከረና እያደገ መሄዱን በየጊዜው ማረጋገጥ።

28.2.10 አገልግሎቱን ሊያግዝ የሚችል ከአዋቂዎችና ከወጣቶች መካከል ፈቃደኛና የተሰጡ አባሎችን ከምዕመናን መካከል በመምረጥ ኮሚቴ (Team) ማቋቋም። ለእነርሱም በቂ ስልጠና በመስጠት ለአገልግሎቱ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ።

28.2.11 ዓመታዊ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለሽማግሌ ቦርድ እና ለዋናው መጋቢ ማቅረብ። በእቅዱም ውስጥ ለወጣቶች የሚሰጠው ትምህርት (Curriculum) ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች (Events) ሪትሪትና የወንጌል ሥርጭት የመሳሰሉትን ማካተት።

28.2.12 የወጣቶችን አገልግሎት በተመለከተ በዕቅዱ መሠረት የተከናወኑትንና ያልተከናወኑትን የሥራ አፈጻጸም በዓመት ሁለት ጊዜ ሪፖርት ለሽማግሌዎች ቦርድ ያቀርባል።

28.2.13 ተተኪውን ትውልድ የሚመራና የሚያሳድግ ለሃላፊነትም የሚያዘጋጅ ለራሱም ልምድ ለመቅሰም ስለሚረዳው ለሽማግሌ ቦርድ በቀጥታ መረጃ መስጠት ስለሚችል ድምጽ አልባ በመሆን በሽማግሌ ቦርድ ስብሰባ ላይ መሳተፍ።

## አንቀጽ 29

## የወጣት መጋቢ ብቃትና ችሎታ

29.1 የወጣቶች መጋቢ ሹመትና መብት በአንቀጽ 22 እንደተጠቀሰው ይሆናል።

29.2 ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኙ የተቀበለና ወጣቱን ትውልድ ለማገልገል መለኮታዊ ጥሪ ያለው፥ ኤፌ 4:11፥ የሐዋ ሥራ 20:28፥ የሐዋ ሥራ13:1-2፥ 1ኛ ቆሮ 12:28፥ ዮሐ 21:15-17

29.3 እንደ እግዚአብሔር ቃል መስፈርትን የሚያሟላ፥ 1ኛ ጢሞ 3:1-7፥ ቲቶ 1:6-9፥ 1ኛ ጴጥ 5:1-4፥ 1ኛ ጢሞ 1:1-7

29.4 ቢያንስ ከ5 ዓመታት በላይ ለማገልገል ፈቃደኛና እራሱን የሰጠ ሊሆን ይገባዋል።

29.5 ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ላላወቁና ላልሰሙ ወንጌልን ለማሠራጨት ሸክም ያለው፥ ማቴ 18:12-14

29.6 ጤናማ ትምህርት በመስጠት ወጣቶችን የሚንከባከብና የሚያሳድግ፥ 1ኛ ጢሞ 5:1-4፥ 5:17፥ 4:16፥ 6:9-12፥ ቲቶ 1:9፥ 2:7-8፥ 1ኛ ጴጥ 5:17፥

29.7 በቤተክርስቲያኒቱ መሠረተ እምነት በሙሉ የሚያምንና የመተዳደሪያ ድንቡንም ተቀብሎ የሚያከብር።

29.8 በየትኛውም የአገልግሎት ዘርፍ ተሰጥዖና ዝንባሌ ያላቸውን ወጣቶች ተተኪ መሪዎች እንዲሆኑ ለማብቃት ራዕይ ያለውና አስፈላጊውንም እገዛ የሚያደርግ።

29.9 መለኮታዊ ጥሪው እንደተጠበቀ ሆኖ በትምህርተ መለኮት ቢያንስ በክርስትና ትምህርትና በወጣት አገልግሎት (Christian education or youth ministry) የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው እንዲሁም በእንግሊዘኛ ቋንቋ በቂ ችሎታ ያለው ሊሆን ይገባዋል።

29.10 መልካም የአገልግሎት፥ የህይወትና የቤተሰብ ምሥክርነት ያለውና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል። ቢቻልም ያገባ ቢሆን ይመረጣል።

29.11 በቅድስና በመኖር ለሌሎች ምሳሌ መሆን የሚችልና ነቀፋ የሌለበት።

29.12 በሌላው ሥር ሆኖ ተቀምጦ ለመማር ፈቃደኛ የሆነ፥

## አንቀጽ 30

## ከሥራ የመገለል ሁኔታዎች (ምክንያቶች)

30.1 የወጣቶች መጋቢ በፈቃዱ ኃላፊነቱን ለመልቀቅ ቢፈልግ ጉዳዩን ለሽማግሌዎች ቦርድ ከ90 ቀናች በፊት በማቅረብ ይኸው ሁኒታ በሽማግሌዎች ቦርድ ከተጠና በኋላ ከሃላፊነቱ መሰናበት ይችላል።

30.2 የወጣቶች መጋቢ ያለ በቂ ምክንያት በመደጋገም ከሥራ ገበታው ላይ ሳይገኝ ቢቀር የሽማግሌዎች ቦርድ በቅድሚያ ችግሩን በመጠየቅ በመምከር በመገሰጽና በማስጠንቀቅ ምክንያቱን አጢኖ ውጤቱ ካልተሻሻለ

በመጨረሻ የደረሰበትን ውሳኔ 2/3ኛው እጅ ከደገፈ ከአረኝነት ሥራው ይሰናበታል፥ ሁኔታውም ለምዕመን ይገለጻል። ኤር 48:10፥ 23:2፥ 1ኛ ሳሙ 16:1፥ ነህ 13:7-9

30.3 የወጣቶች መጋቢ የቤተክርስቲያኒቱን ሕግ ሲተላለፍ የሞራል ውድቀት ወይም የእምነት ግድፈት ሲገኝበት ወዲያው ከወጣቶች መጋቢነት ሥራው ይገለላል ይህም ውሳኔ ለምዕመኑ ይገለጻል።

30.4 የወጣቶች መጋቢ በተሰጠው ውሳኔ ባይስማማ ከቤተክርስቲያኒቱ ምዕመን የተውጣጡ ልዩ ኮሚቴ ተቋቁሞ ሁኔታውን እንዲያዩ ይደረጋል።

30.5 የሽማግሌዎች ቦርድ እንደ አስፈላጊነቱ የተሰናበተውን የወጣቶች መጋቢ በሕይወቱ ተሐድሶ እንዲያገኝ የሚችለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል።

## አንቀጽ 31

## አባልነት

አባልነት፡-

31.1 የቤተክርስቲያኒቱ አባል የሚሆኑ ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው የተቀበሉ፥ የውኃ ጥምቀት የወሰዱ፥ የቤተክርስቲያኒቱን መሠረተ እምነትና የመተዳደሪያ ደንቡን በሙሉ የተቀበሉ ናቸው።

31.2 ከሌሎች ቦታ የመጡ ከሆነ ይህን የሚያስረዳ የመሸኛ ደብዳቤ ከመጡበት ቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቡ መሆን አለባቸው።ማቅረብ የማይችሉበት አሳማኝ ሁኔታ ካለ ቢያንስ አማኙን የሚያቅ ሁለት ምስክሮች ስለህይወቱ ይጠየቃሉ።

## አንቀጽ 32

## የአባልነት መብትና ግዴታ

32.1 ማንኛውም የቤተክርስቲያኒቱ አባል ስለ ቤተክርስቲያኒቱም ሆነ ራሱን በሚመለከት ጥያቄ፥ ቅሬታዎችንና የተለያቱ ኃሳቦችን በቃልም ቢሆን በጽሑፍ ለሽማግሌዎች ቦርድ ማቅረብ ይችላል።

32.2 ምርጫ በሚያስፈልገው የቤተክርስቲያን ጉዳይ ውስጥ እንደ እግዚአብሔር ቃልና ቤተክርስቲያኒቱ ባላት የምርጫ ሥነስርዓት መሠረት ተመርጦ የማገልገልና መርጦ የመገልገል መብት አለው።

32.3 የጋብቻ፤ ሕፃናትን ለጌታ የማስረከብና የቀብር ሥነስርዓት የመጠየቅና እንደ እግዚአብሔር ቃልና ኃሳብ አገልግሎትን የማግኘት መብት አለው።

32.4 የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢና ሽማግሌዎች እንዲጸልዩበት በተለይም በህመም ጊዜ የመጠየቅ መብት አለው።

32.5 ከቤተክርስቲያኒቱ ግንኙነት አንጻር እንደአስፈላጊነቱ ማስረጃ የመጠየቅ መብት አለው።

32.6 በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ባሉት ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የመገልገልና ከእግዚአብሔር በተቀበለው (በተቀበለችው) ጸጋ ቤተክርስቲያኑ ስታሰማራ የማገልገል መብት አለው።

32.7 በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ደህንነት የተቀበለ ወይም የተለወጠ ክርስቲያን መሆን አለበት። ዮሐ 1:12-14፥ ሮሜ 10:9-10፥ ኤፌ 2:8-10፥ የሐዋ ሥራ 2:38-42

32.8 በዚህ ቤተክርስቲያን ለአባልነት የበቁ ሁሉ በሕዝቡ ፊት የአባልነት ሥነስርአት ይፈጽማሉ።

32.9 ማንኛውም የቤተክርስቲያኒቱ አባል ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር በምድር ላይ ያስቀመጣት ወኪል ስለሆነች ለቤተክርስቲያን ሥልጣን የመገዛትና የመታዘዝ ግዴታ አለበት።

32.10 ማንኛውም የቤተክርስቲያን አባልና አገልጋይ (በአንቀጽ 3.10.2.2. እንደተጠቀሰው) የሌላ ቤተክርስቲያን በቋሚነት አባልና አገልጋይ መሆን አይችልም።

32.11 የአንድ የቤተክርስቲያን አባል ተቀዳሚና የመጀመሪያ ኃላፊነቱ የራሱን ሕይወት መጠበቅ ነው። ገላ 6:5

ሀ) በቅድስና በመኖር ለሌሎች መልካም ምሳሌ መሆን። 2ኛ ቆሮ 6:14-18

ለ) በጤናማና በትክክለኛው የወንጌል ትምህርት መኖር። 2ኛጢሞ 2:132.12

32.12 በጸሎት፥ የጌታን ራት በመውሰድ፥በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ያሉትን የመጽሃፍ ቅዱስ ሳምንታዊ ትምህርቶች መካፍል እንዲሁም ስብሰባዎችን በመካፈል በሚያሳየው ሕብረት ከቅዱሳን ጋር በፍቅርና በመተሳሰብ መኖር። 1ኛ ቆሮ 11:23-30፥ ማቴ 26:26-29፥ የሐዋ ሥራ 2:42

32.13 ቤተክርስቲያኒቱን በሁለንተናው ማለትም በጸሎት፥ በኃሳብ፥ በእውቀት፥ በጉልበትና በአስራት በማገልገል ለማህበረ ምዕመናን እድገትና ለቤተክርስቲያን መታነጽ ድርሻውን መፈጸም። ሮሜ 12:4-8፥ 2ኛ ቆሮ 9:7፥ ሉቃስ 8:3

32.14 በቤተክርስቲያን ተመርጠው በመንፈስ ቅዱስ ተሰይመው አገልግሎት የሚሰጡትን አገልጋዮች ምክርና ተግሳጽ እንዲሁም ውሳኔ በፍቅር መቀበል። 1ኛ ጢሞ 5:20-21

32.15 በውጭ ባሉት ሰዎች ፊት መልካም ምስክርነት ያለው ሕይወትና ተግባር ማሳየት። 1ኛ ጴጥ 2:9-10

32.16 አንድ አባል በእግዚአብሔር ቃል ሕይወቱን የመምራትና የማስተዳደር ልጆቹንም እንደ እግዚአብሔር ቃል የማሳደግ ኃላፊነት አለበት ኤፌ 6:4፥ 1ኛ ጢሞ 3:4-7

32.17 ከሌሎች ምዕመናን ጋር በፍቅር በመኖር የመንፈስ ህብረትንና አንድነትን ሳያሰልስ መጠበቅ።

32.18 ማንኛውም አባል ከቤተክርስቲያኒቱ ዋና ተልዕኮ ማለትም በማቴ 28:19-20 በተገለጸው መሠረት ለተግባራዊነቱ በመስጠት ተባባር ሊሆን ይገባዋል።

32.19 አንድ አማኝ የቤተ ክርስቲያኔቱ አባል የሚሆነው የአባልነቱን ፎርም ሞልቶና መተዳደሪያ ደንቡን መቀበሉን በመተዳደሪያ ፎርሙ ላይ ፊርማውን ሲያሰፍር ይሆናል።

## አንቀጽ 33

## ከአባልነት የመገለል (የመሰረዝ) ምክንያት

33.1 በአንቀጽ 11.19 እና 11.20 መሠረት አንድ አባል የቤተክርስቲያኒቱን የመተዳደሪያ ደንብና መሠረተ እምነት ሲተላለፍና የሞራል ውድቀት ሲገኝበት **በቅድሚያ በዋና መጋቢ አማካኝነት አስፈላጊውን ምክር፥ ትምህርትና የጸሎት ድጋፍ ተደርጎለት ለውጥ ከሌለው** በሽማግሌዎች ቦርድ በቅድሚያ ችግሩን በመጠየቅ ከተመከረ፥ ከተገሰጸ፥ በቤተክርስቲያን ከሚሰጡት አገልግሎቶችና በቤተክርስቲያን ከሚሰጡት ስርዓቶች ከታገደ በኋላ በዚህ ሁሉ
ካልተመለሰ በመጨረሻ ከተገኙት የቦርዱ አባላት 2/3 ከደገፈው ከአባልነቱ ይሰናበታል። ይህም ለምዕመናን በስብሰባ ላይ ይገለጻል። 1ኛ ቆሮ 5:1-5፥ ማቴ 18:15-17፥ 2ኛ ቆሮ 2:5-10

33.2 አንድ አባል ያለ በቂ ምክንያት ከሁለት ወር በላይ በማከታተል ከቤተክርስቲያን ወይም ከቤተክርስቲያን ሕብረት ቢቀር ችግሩ ከተጠየቀ ከተመከረና አስፈላጊው ማበረታቻ ከተሰጠው በኋላ ምንም ለውጥ ካላሳየ ጉዳዩ በሽማግሌዎች ቦርድ ተጠንቶ ከአባልነት እንዲሰረዝ ይደረጋል።

33.3 አንድ አባል የቤተክርስቲያኒቱን ሰላምና አንድነት ሆን ብሎ የሚያናጋ ድርጊቶችን ሲፈጽም ቢገኝ በቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ቦርድ ተመክሮ የማይመለስ ከሆነ ከአባልነት ይሰረዛል።

## አንቀጽ 34

## የአስተዳደር ፋይናንስና የገንዘብ ያዥው የሥራ ኃላፊነትና ተግባር

የሂሳብ ሹሙና ገንዘብ ያዡ የሚመረጡት በድምጽ ብልጫ ከሽማግሌዎች መካከል ይሆናል።

34.1 የገንዘብ ያዢው የሥራ ኃላፊነት

34.1.1 የቤተክርስቲያኒቱን ገንዘብ ይይዛል።

34.1.2 ልዩ ልዩ የቤተክርስቲያኒቱን ገቢዎች ተረክቦ በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ ባንክ ገቢ ያደርጋል።

34.1.3 የቤተክርስቲያኒቱ የሽማግሌዎች ቦርድ ባጸደቀው መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል።

34.1.4 የቤተክርስቲያኒቱን የሂሳብ ወጪና ገቢ ሰነዶችን ለአስተዳደር ፋይናንስ ያስረክባል።

34.2 አስተዳደርና ፋይናንስ፡

34.2.1 የቤተክርስቲያኒቱን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ወጪና ገቢ መዝገቦችን ይይዛል የበላይም ሆኖ ይቆጣጠራል።

34.2.2 የወጪና የገቢ ደረሰኞችን በጥንቃቄ ያስቀምጣል።

34.2.3 የቤተክርስቲያኒቱን የገንዘብ አቋም በመደበኛው ወርኃዊ የሽማግሌዎች ቦርድ ስብሰባ ላይ ያቀርባል።

34.2.4 በሽማግሌዎች ቦርድ ትዕዛዝ መሰረት በቤተክርስቲያኒቱ ስም ተመዝግበው ያሉትን ገንዘብና የተለያዩ ንብረቶችን በተገቢው ቦታ መዋላቸውንና በጥንቃቄ መያዛቸውን ያረጋግጣል።

34.2.5 የቤተክርስቲያኒቱ ወጪዎች እንደ አስፈላጊነታቸው በተገቢው ቦታ በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

34.2.6 በሽማግሌዎች ቦርድ በሚጠየቅበት ጊዜ የሒሳብ መዝገቡን ለምርመራ ያቀርባል።

34.2.7 በዓመት ሁለት ጊዜ በሚደረገው የአባላት አጠቃላይ ስብሰባ ላይ የቤተክርስቲያኒቱን ገንዘብ ነክ ሪፖርት ያቀርባል።

34.2.8 የቤተክርስቲያኒቱን የሂሳብ ወጪ ሰነዶችን ጸሃፊው ከምክትል ሰብሳቢው ጋር በመሆን ያንቀሳቅሳል።

34.2.9 በሀገሪቱ ደንብ መሠረት የቤተክርስቲያኒቱን ሠራተኞች ጥቅማ ጥቅሞችን እየተከታተለ አስፈላጊ ነገሮችን ያስፈጽማል።

## አንቀጽ 35

## የመረዳጃ እድር

**35.1 የዚህ የመረዳጃ ዕድር አባላት የሚተዳደሩበት በወጣው የውስጥ የመተዳደሪያ ደንብ ይሆናል።**

**35.2 የገንዘብ አቀማመጥ በቤተክርስቲያኒቱ ስም ለብቻው የተለየ የሂሳብ ቁጥር (Account) ይኖረዋል።**

**35.3 ገንዘብ ወጪ የሚሆነው በዕድሩ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ጠያቂነት ቀርቦ በቤተክርስቲያኒቱ አሰራር ይሆናል።**

**35.4 የመረዳጃ ዕድር ተጠሪነቱ ለሽማግሌዎች ቦርድ ይሆናል።**

## አንቀጽ 36

## የገንዘብ አያያዝና አወጣጥ

36.1 የቤተክርስቲያኒቱን የገቢ ምንጭና የወጪ ዓይነት

1) የገቢ ምንጭ፡-

ሀ) አስራት ሚልክ 3:10፥ ዘሌ 27:30፥ ዘዳግ 12:17፥ 14:22

ለ) በኩራት ነህም 10:35-37፥ ሕዝ 20:40

ሐ) መባ 2ኛ ነገ 12:10፥ ሉቃስ 21:1-4

መ) ውርስ

ሠ) ስጦታ

ረ) እንዳስፈላጊነቱ (Fund Raising)

2) የቤተክርስቲያን ወጪ፡-

ሀ) ለወንጌል አገልግሎት ስርጭት አቅሟ እንደፈቀደ መጠን ታወጣለች።

ለ) ለአገልጋዮችና ለሰራተኞች ደመወዝ ትከፍላለች።

ሐ) ለተቸገሩ እርዳታና ስጦታ ታደርጋለች።

መ) ለስልክ ለፋክስ ለኢንተርኔት ለመብራት ለውኃ ለኢንሹራንስ ለመሳሰሉት ወጪ ታደርጋለች።

ሠ) ለቋሚና ለአላቂ እቃዎች መግዣ ወጪ ታደርጋለች።

ረ) የሕንፃ እደሳ

36.1 የቤተክርስቲያኒቱ ገንዘብ በቤተክርስቲያኒቱ ስም በባንክ ይቀመጣል።

36.2 የሽማግለዎች ቦርድ በሚወስነውና በሚያጸድቀው መሰረት ማንኛውም ከ$200.00 በላይ የሆነ የቤተክርስቲያኒቱ የገንዘብ ወጪ የሚደረገው የሒሳብ ሹሙ፥ የሰብሳቢው ወይም የጸሐፊው ፊርማ ሲኖርበት ነው። ሰብሳቢው ወይም ጸሐፊው በሌለበት ጊዜ ለባንክ የተወከለው ሽማግሌ መፈረም ይችላል፥ ሆኖም ከ$200.00 በታች ለሚሆነው ወጪ የሒሳብ ሹሙ ብቻ ይፈርማል።

36.3 የቤተክርስቲያኒቱ የበጀት ዓመት ከጀንዋሪ 1 እስከ ዲሴንበር 31 ይሆናል።

## አንቀጽ 37

## የሒሳብ ምርመራ

37.1 ቤተክርስቲያኒቱ እንደ አስፈላጊነቱ በውስጥና በውጭ የሒሳብ መርማሪዎች ሒሳቧን በዓመት አንድ ጊዜ አስፈላጊም ከሆን ከዚያ በፊት ታስመረምራለች። የሒሳብ መርማሪዎቹም ይህንኑ ሪፖርት ለጠቅላላው ጉባኤ ያቀርባሉ።

37.2 ቤተክርስቲያኒቱ የምትወክላቸው የውስጥ ሂሳብ መርማሪዎች፡-

1) የቤተክርስቲያኒቱ አባሎች መሆን አለባቸው

2) የሂሳብ ሥራ (Accounting) ዕውቀትና ችሎታ ያላቸው መሆን አለባቸው

3) በቁጥር ከሶስት የሚያንሱ መሆን ይኖርባቸዋል

4) በቤተክርስቲያኒቱ የሽማግለዎች ቦርድ ይመረጣሉ

5) ከሌላ ስፍራ የመጡ ከሆኑ በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ለአንድ ዓመት ያህል የቆዩ እንዲሁም ከመጡበት ቤተክርስቲያን ስለማንነታቸው የተመሰከረላቸው ሊሆኑ ይገባል።

6) የአንድ ሂሳብ መርማሪ የአገልግሎት ዘመን ሶስት ዓመት ቢሆንም በአገልግሎት ዘመኑ መጨረሻ እንደገና ለሁለት ዓመት ለመመረጥ ይችላል። ሆኖም ለሦስተኛ ዘመን ምንም እንኳን ለሥራው አስፈላጊ ቢሆንም አንድ የአገልግሎት ዘመን ማረፍ አለበት።

7) የውጭ ሂሳብ መርማሪዎች በሚያደርጉት የሂሳብ ምርመራ ለሚነሳው ማንኛውም ሂሳብ ነክ ጥያቄ መልስ ይሰጣሉ።

## አንቀጽ 38

## ደንቡን የማሻሻል ይዘት

በዚህ የቤተክርስቲያኒቱ መተዳደሪያ ደንብ ከተዘረዘሩት ውስጥ መሰረተ እምነቱ ምን ጊዜም የማይሻሻልና የእግዚአብሄር ቃል ስለሆነ የማይለወጥ መሆኑን ታምናለች። አንቀጾች ውስጥ የተዘረዘሩት ማናቸውም ደንቦች ወይም ቁጥር በማናቸውም ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ በቤተክርስቲያኒቱ የሽማግለዎች ቦርድና በአባሎች 3/4 ኛ እጅ ከተደገፈ ሊሻሻል ሲለወጥ ወይም ሊሰረዝ ይችላል።

## አንቀጽ 39

## ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

የሽማግለዎች ጉባኤ ደንቡን እንዲያፀድቅ የአባላት ጉባኤን ይጠራል። ከጉባኤውም 3/4ኛው እንዲገኝ ይደረጋል፥ በደንቡም 2/3ኛው ከፀደቀ ያልፋል ሆኖም 3/4ኛው ካልተገኘ አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ ስብሰባ ይጠራል በተገኙትም አባላት 2/3ኛው ካሳለፈ ይፀድቃል።

## አንቀጽ 40

## ትርጉም

በዚህ ውስጠ ደንብ ላይ የትርጉም ልዩነት ቢነሳ ቋሚ የሚሆነው የትርጉም ውሳኔ የሚሰጠው በቤተክርስቲያኒቱ የሽማግለዎች ቦርድ ይሆናል።

## የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ኅብረት ቤተክርስቲያን በካንሳስ

## የመተዳደሪያ ደንብ የግምገማ ቅጽ

በሚከተሉት ተራ ቁጥር አንቀጹን በመጻፍ አስተያየቶን ሊሰጡ ይችላሉ።

| ተ.ቁ | አንቀጽ | አስተያየት |
|---|---|---|
| 1. | | |
| 2. | | |
| 3. | | |
| 4. | | |
| 5. | | |

የገምጋሚ ስም ______________________________ ፊርማ ____________________